# ኦሪት ዘፀአት (58)

## ጥናት አንድ ዘፀአት 1፡1-22

የጥናት ዓላማ፡- እነዚህ ሁለት ሴቶች በህይወታቸው ቆርጠው በፈርዖን የታዘዙትን ትዕዛዝ ላለመፈጸም እንደወሰኑ ሁሉ፤ ዛሬም እኛ ከእግዚአብሄር ቃል ጋራ የሚቃረነውን ማናቸውንም የሰዎች ትዕዛዝ ለማድረግ ስንታዘዝ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሄር ቃል መታዘዝ እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አዋላጆቹ ግን እግዚአብሄርን ስለፈሩ የግብጽ ንጉስ ያዘዛቸውን አልፈጸሙም፤ ወንዶቹንም ልጆች በህይወት እንዲኖሩ ተዋቸው።" ዘጸዓት 1፡17

1. ዘጸ 1፡1-22 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-7 ውስጥ ስናነብ እግዚአብሄር አምላክ ከብዙ ጊዜያት በፊት ቁጥራቸው እንደ ባህር አሸዋ እንደሚሆን ለባርያው ለአብርሃም የገባለት ቃል በግብጽ ምድር ውስጥ የተጀመረው በስንት ሰዎች ነበረ? እግዚአብሄር ለወዳጁ ለአብርሃም የገባለትን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ከተጠቀመባቸው መንገዶች መካከል ቢያንስ አንደኛውን በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ማየት እንችላለን፤ ይህ እግዚአብሄር ተጠቀመበት ማለት የምንችለው መንገድ ምን እንደሆነ ተናገር።
2. በቁ8 ላይ "በግብጽም ስለ ዮሴፍ የማያውቅ አዲስ ንጉሥ ነገሰ።" በማለት ሲናገር፤ ይህ ማለት የነገሰው ንጉሥ ዮሴፍ የተባለ ሰው በግብጽ ምድር ላይ እንደነበረ አልሰማም ለማለት ነው ወይስ ጸሐፊው ይህንን ሲል ምን ለማለት የፈለገ ይመስልሃል? የእስራኤል ሕዝብ በቁጥር እየጨመሩና እየበዙ መሄዳቸው በአዲሱ ንጉስ ውስጥ ፍርሃትን እንደፈጠረበት ከቁ9 እና ከቁ10 መረዳት እንችላለን፤ ታዲያ ይህ ንጉስ በውስጡ የተፈጠረው ፍርሃትና ለሕዝቡ መፍትሄ አድርጎ ያቀረበውስ ነገር ምን የሚል ነበረ?
3. በቁ8-10 ውስጥ ስናነብ ይህ በግብጽ ላይ የነገሰው አዲስ ንጉስ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት አመራር ውስጥ የሚተዳደሩ አገሮች የማይገጥማቸውና ነገሥታቱ የማያደርጉትን አንድ ነገር ሲያደርግ እናየዋለን፤ ይህ አንድ ነገር ምንድነው? ንጉሱ ለአገሪቱ ችግር ይሆናል ብሎ አርቆ ለተመለከተውና ለህዝቡ ለተናገረው ችግር መፍትሄ ሆኖ ያገኙትን ነገር በቁ11 ላይ በሥራ ላይ ውሎ እናያለን፤ ይህ ለታያቸው ችግር እንደ መፍትሄ ሆኖ ሥራ ላይ የዋለው ነገር ምን ነበረ?
4. ቁ12-14ትን ስትመለከት ግብጻውያኑ ችግር ይሆናል ብለው የገመቱትና የፈሩት የእስራኤላውያኑ የመብዛታቸው ጉዳይ መፍትሄ ይሆናል ብለው የወሰዱባቸው እርምጃዎች ምን ያህል የታሰበላቸውን ግብ መትተዋል ብለህ ታምናለህ? አንዳንድ ጊዜ ጠላታችን በሕይወታችን ፍሬአማ ሆነን በመገኘታችን ተናዶ የሚወስደውን የበቀል እርምጃ፤ እግዚአብሄር አምላካችን ደግሞ መልሶ የበለጠ ፍሬአማ የምንሆንበት መንገድ አድርጎ ሊጠቀምበት እንደሚችል መማር እንችላለን።
5. የግብጽ ንጉስም ሆነ ግብጻውያኑ የእስራኤል የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት የመጨመር ሁኔታ ስላስደነገጣቸው በእስራኤላውያኑ ላይ ከወሰዱት በቁ11-14 ባሉት ክፍሎች ውስጥ ከምናየው መፍትሄ በተጨማሪ ለእስራኤላውያኑ ቁጥር መጨመር በመፍትሄነት በቁ15-16 ላይ ሲወስዱት የምንመለከተው ዋነኛ ሃሳብ ምን ነበረ? ለምን ይመስልሃል የግብጽ ንጉስ በቁ15-16 ውስጥ የሰፈረውን ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ ወንዶች ብቻ ተገድለው ሴቶቹ በህይወት እንዲኖሩ የሚለውን ሃሳብ ያስተናገደው?
6. ቁ19-21ድን ስናነብ አዋላጆቹ በግብጻዊያን ሴቶችና በእብራዊያን ሴቶች መካከል ልዩነት እንዳለ አድርገው ነው ለንጉሱ ምክንያታቸውን ሲሰጡ የምንሰማው። እነዚህ አዋላጆች በሁለቱ ዓይነት ሴቶች መሃል ያለው ልዩነት ምንድነው ብለው ነው የሚናገሩት? እነዚህ በዚህ ሥፍራ ላይ የምናያቸው አዋላጆች እግዚአብሄርን በመፍራትና የንጉሥን ሕግ ከመታዘዝ እንቢ በማለታቸው ምክንያት የሆነላቸውን ሁለት ነገሮች ማየት እንችላለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሄርን በመፍራት ሕጉን መጠበቅ በሕይወታችን በረከትን ሊያመጣ እንደሚችል መገንዘብ ይኖርብናል።
7. ቁ19-22ትን ላይ ስንመለከት ንጉሱ እስካሁን ችግሩን ለመፍታት የወሰዳቸው እርምጃዎች ተፈላጊውን ግብ እንዳልመቱለት የሚጠቁመን የትኛው ሃሳብ ነው? የወሰዳቸው መፍትሔዎች እንዳልሰሩ ባወቀ ጊዜ የወሰደው ቀጣይ እርምጃ ምን ነበረ?
8. ወደ ኋላ መለስ ብለን በቁ17-19 ውስጥ የተካሄደውን ነገር ጠለቅ ብለን ስንመለከት፤ በምን መንገድ ነው የእነዚህ ሁለት ሴቶች ድርጊት በሐዋ ሥራ 5፡29 ላይ ከሚገኘው የሐዋርያቱ አነጋገር ጋራ አንድ ሆኖ የሚገኘው? አንተስ በህይወትህ አለቃህ ወይም ደግሞ ባለሥልጣን የሆነ ሰው ከእግዚአብሄር ቃል ጋራ ተቃራኒ ነገር እንድታደርግ ቢነግርህ የሴቶቹን ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ነህ ወይ? ማናቸውንም ከእግዚአብሄር ቃል ጋራ የሚቃረን ነገር እንድናደርግ ስንጠየቅ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሄር ቃል መታዘዝ ይጠበቅብናል።

# ጥናት ሁለት ዘፀአት 2፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- የሙሴ ቤተሰቦች በእግዚአብሄር ላይ ያሳዩት እምነት ከልጃቸውም አልፎ ለእስራኤል ሁሉ ደህንነትንና ብሎ ነጻነትን እንዳስገኘላቸው ሁሉ፤ እኛም በእግዚአብሄር ላይ የምናሳየው ጠንካራ እምነት ከራሳችን አልፎ ለብዙዎች በረከትና የደህንነት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ መልከ መልካም ሕጻን መሆኑን ስላዩ በእምነት ሶስት ወር ሸሸጉት፤ የንጉሱንም አዋጅ አልፈሩም።" ዕብራዊያን 11፡23

1. ዘጸ 2፡1-25 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ውስጥ ከምናነባቸው ነገሮች ብቻ በመነሳት በዚህ ክፍል ስለተወለደው ወንድ ልጅ ማንነት ማወቅ የምንችላቸው ነገሮች ምንድናቸው? ከእነዚህ ጥቅሶች ወጣ በማለት ዘጸ 6፡20ን ስናነብ በዚህ ሥፍራ ሲወለድ የምናገኘው ሕጻን ልጅ አባትና እናት ስም ማንና ማን ይባላል?
2. በምዕራፍ 6 ውስጥ ከተመለከትነው ጥቅስ በመነሳት፤ በዘጸ 2፡4 ላይ እህቱ እንደሆነች የምንመለከታት ወጣት ስሟ ማን ይባላል? እነዚህን አራት ቁጥሮች በምናነብበት ጊዜ እነዚህ ቤተሰቦች በሕጻኑ ላይ ሊመጣ ከሚችለው ነገር ሁሉ ሊከላከሉለት በተለይም ደግሞ ከንጉሱ የሞት ትዕዛዝ ሊያስጥሉት እንደማይችሉ ቢገባቸውም እንኳን ለደህንነቱ ለእግዚአብሄር አሳልፎ ከመስጠት ባሻገር የወሰዷቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች እንመለከታለን፤ በዚህ ክፍል የምናያቸው የወሰዷቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች ምን ምንድናቸው? አንተስ በህይወትህ ነገሮችን ለእግዚአብሄር አሳልፈህ ስትሰጥ፤ በአንተ በኩል ማድረግ የሚገባህን ነገሮች ታደርጋለህ ወይ?
3. በዚህ ምንባብ ውስጥ ሶስት ወር ብላቴናውን እንደሸሸጉት የምንመለከት ሲሆን፤ እብ 11፡23ትን በተጨማሪ ስንመለከት ግን የእነዚህ ወላጆች ልጁን የመሸሸግ ጉዳይ ከዚያ ያለፈ ትርጉም እንደነበረው እንረዳለን፤ ታዲያ ያ ትርጉም ምንድነው ትላለህ? በቁ1-4 ውስጥ ያለው ታሪክ የልጁ ቤተሰቦች እርሱን ለማዳን በነበራቸው ፍላጎት የተነሳ ያደረጓቸው ነገሮች ናቸው ብንልና፤ በቁ5 እና በቁ6 ውስጥ የምናየው ደግሞ እግዚአብሄር የዚህን ልጅ ሕይወት ለማዳን ያደረገው ነገር ነው ቢባል፤ እነዚህ ሁለት ቁጥሮች እግዚአብሄር ስለዚህ ልጅ ለመጠንቀቅ አድርጎታል ማለት የሚያሰኙንን ነገሮች በመጥቀስ ለመናገር ሞክር።
4. ቁ7-10 ላይ ያለውን ሃሳብ ስንመለከት እግዚአብሄር አምላክ በምን መንገድ ነበረ ሙሴ የግብጽን ትምህርት ብቻ ተሞልቶ እንዳያድግና የወገኖቹንም ማንነት እንዲያውቅ፣ ከዚያም አልፎ የእስራኤልን አምላክ ማንነት እንዲማር ያደረገው? በቁ10 ላይ "ባደገ ጊዜ" የሚለውና በቁ11 ላይ ደግሞ "ሙሴ ካደገ በኋላ" የሚሉት የተለያዩ የእድሜ ክልልን እንደሚናገሩ የታወቀ ሲሆን፤ በሐዋ ሥራ 7፡23-26 ውስጥ ከእነዚህ ከሁለቱ የትኛውን ወቅት ነው የሚጠቁመን?
5. በቁ11-14 ውስጥ ስናነብ ሙሴ ድርጊቱን ለመፈጸም ማለትም እብራዊውን በመደብደብ ላይ የነበረውን ግብጻዊ ከመግደሉ በፊት አስቀድሞ ያደረገው አንድ ነገር ምን እንደነበረና ለምን ያንን ማድረግ እንዳስፈለገው ጭምር ተናገር። ሙሴ ግብጻዊውን በገደለ ጊዜ ማንም ሰው በአካባቢው እንዳልነበረ ለማረጋገጥ ግራና ቀኙን ተመልክቶ እንደነበረ እናውቃለን፤ ታዲያ ሙሴ ይህንን ያህል ጥንቃቄ አድርጎ ሳለ ቁ15ት ላይ ከምናየው የፈርዖን የሙሴን ድርጊት መስማት ለእኛ ሊያስተምረን የሚችለው ነገር ምንድነው?
6. ሙሴን በግብጽ አገር ተዝናንቶ በንጉሥ ቤት ከሚኖርበት ኑሮው የተፈናቀለበትን ምክንያት እና በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ በቁ16-20 ላይ ሙሴ ሴቶቹን ለማጥቃት የተነሱት እረኞች ለማባረር የወሰደውን እርምጃ ሁለቱንም በምናይበት ጊዜ፤ እግዚአብሔር ከፊት ለፊቱ ያዘጋጀለትን አገልግሎት የሚመስል ልብ ነበረው ለማለት የሚያበቃ ምን ነገር ያሳዩናል? በቁ19 ላይ የሴቶቹ አባት ከጥቃት ስለተከላከለላቸው ሰው ሲጠይቃቸው ሙሴ ግብጻዊ እንደሆነ ነው የተናገሩት፤ ለምንድነው ሙሴ እብራዊ ሆኖ እያለ ሴቶቹ ግብጻዊ እንደሆነ የተናገሩት?
7. በቁ23-25 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ስንመለከት እግዚአብሄር አምላክ ከአብርሃም፣ ከይስሃቅና ከያዕቆብ ጋራ ያደረገውን ቃል ኪዳን እንዳሰበ እናነባለን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ይህንን ቃል ኪዳን እንዲያስብ ምክንያት የሆነው ምን ነገር ታያለህ? ቁ24 ላይ "የጩኸታቸውን ሲቃ ሰማ" እንደገና በቁ24 ላይ ደግሞ "የገባውን ቃል ኪዳን አሰበ"፣ ቁ25 "እስራኤላውያንን ተመለከተ"፣ ቁ25 "ስለ እነርሱም ገደደው" የሚሉትን አነጋገሮች እናያለን። እነዚህን የሃሳብ ቅደም ተከተሎች በመመልከት ለራሳችን ሕይወት ምን አይነት ትምህርትን መቅሰም እንችላለን?
8. በዕብ 11፡23 ላይ የሙሴ ወላጆች በወሰዱት ቆራጥነትና እምነት የተሞላው እርምጃ አስገኝቷል የምትላቸውን አንድ ወይም ሁለት ዋና ዋና ውጤቶች ተናገር። አንተስ በእግዚአብሄር ላይ ከምታሳየው ጠንካራ የማያወላውል እምነትህ የተነሳ ለሌሎችም የሚተርፍ ፍሬ አፍርተህ ታውቃለህ? ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሄር ላይ በመተማመናችንና በእርሱ ማንነት ላይ በመደገፋችን ምክንያት፤ ከራሳችን አልፎ በአካባቢያችን የሚገኙትንም እንኳን ሳይቀር ሊጠቅም የሚችል መልካም ነገር ሊወጣ እንደሚችል መዘንጋት አይኖርብንም።

# ጥናት ሶስት ዘፀአት 3፡1-22

የጥናት ዓላማ፡- "እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" የሚል ማበረታቻ ለሙሴ እንደተሰጠው ሁሉ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ደቀመዛሙርቱ ሰዎችን ከሃጥያት ባርነት ነጻ ለማውጣት ለሰጣቸው የወንጌል አደራ፤ እንዳይፈሩና ለብቻቸው እንዳልሆኑ ያደፋፈረበት መንገድ ለሙሴ እንደተባለው በማቴ 28፡20 "…እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" በማለት ለሁላችንም የሚሆንማበረታቻ እንደተሰጠን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ የማወጣ እኔ ማነኝ? አለው…እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" ዘጸ 3፡11-12

"ያዘዝኳቸውንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" ማቴ 28፡20

1. ዘጸ 3፡1-22 በአንድነት ይነበብ። በተለይ ቁ1 ላይ የምናነበው ነገር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣው ሰውና፤ በሌላ በኩል ደግሞ የዓለምን ሕዝብ ከሃጥያት ባርነት ነጻ ያወጣው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሳሰሉበትን አንድ እውነት ይጠቁመናል፤ ይህ እውነት ምን እንደሆነ ተናገር። ማናቸውም በምድረበዳ ላይ የሚገኝ ቁጥቋጦ በተለያየ ምክንያት በእሳት ሊቃጠል ይችላል፤ ታዲያ በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይም በቁ2-3 ላይ የሚነደውን ቁጥቋጦ ልዩ የሚያደርጉትን ቢያንስ ሁለት ነገሮች ተናገር።
2. በቁ4 ላይ ስንመለከት ሙሴ ቁጥቋጦው በእሳት መንደዱ ነገር ግን ተቃጥሎ አለማለቁ አስገርሞት ለማየት ጠጋ ባለበት ሰዓት ነበረ እግዚአብሄር የሚፈልገውን ሃሳብ ማስተላለፍ የፈለገው። ለምን ይመስልሃል ሙሴ እሳቱ ወደሚናድበትና እግዚአብሄር ወደሚገኝበት አቅጣጫ ከመጠጋቱ በፊት መናገር ያልፈለገው? በዚህ ሥፍራ ላይ በምናየው ሙሴ በተመለከተው ተዓምራትና ወደ ተመለከተው ነገር በተጠጋ ጊዜ መስማት የቻለውን የእግዚአብሄርን ድምጽ በማጤን ከእኛ ሁኔታ ጋራ ሊዛመድ የሚችልበት መንገድ ይታይሃል ወይ? መልስህን ለወገኖች ለማስረዳት ሞክር።
3. በቁ4 ላይ ስንመለከት ሙሴ ተአምራቱን ተመልክቶ በበለጠ ጠጋ በማለት ለማየት ወደ ቁጥቋጦው በተጠጋ ጊዜ የተከሰተ አንድ ሌላ ተአምራት እንደነበረ እንመለከታለን፤ በዚህ ሥፍራ ለሙሴ አስቀድሞ ከገጠመው አስገራሚ ተአምራዊ ሁኔታ አልፎ እግዚአብሄር በሙሴ ህይወት ያደረገው ሌላ ተጨማሪ ተዓምራት ምን ነበረ ትላለህ? በቁ5-7 ውስጥ ስንመለከት እግዚአብሄር አምላክ ለሙሴ ማንነቱን ሲያስተዋውቅ የተጠቀመበት የማስተዋወቂያ መንገድ ምን የሚል ነበረ?
4. በቁ7 ላይ "አይቻለሁ"፣ "ሰምቻለሁ"፣ "ተረድቻለሁ" በቁ8 ላይ "ወርጃለሁ" እና በቁ10 ላይ ደግሞ "እልክሃለሁ" የሚሉትን ቃላት በምናነብበት ጊዜ፤ እነዚህ ቃላቶች ሁሉ ትኩረታቸው ወደ አንድ አቅጣጫ እንደሆነ እንረዳለን። የቃላቶቹ ሁሉ ትኩረት በማን ላይ እንደሆነ ነው የምንመለከተው? እንደነዚህ ቁጥሮች አነጋገር፤ ሊሆን ባለው ነገር ላይ ማለትም ከግብጽ ባርነት ነጻ መውጣታቸውን አስመልክቶ የእስራኤል ህዝቦች ሊኖራቸው ስለሚገባው ተሳትፎ ከዚህ ክፍል የምንረዳው ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል ውስጥ የምናየው ሁኔታ ከእኛ ደህንነት ወይም ከሰይጣን ባርነት ነጻ ከመውጣታችን ጋራ በምን መንገድ ይመሳሰላል?
5. ቁ11-15 ላይ በምናነብበት ጊዜ ሙሴ ሕዝቡን ያድን ዘንድ ወደ ግብጽ እንዲሄድ ከእግዚአብሄር ለመጣለት ትዕዛዝ ሁለት የተለያዩ ጥያቄዎችን ሲያቀርብለት እናያለን፤ እነዚህ ሁለት ሙሴ ለእግዚአብሄር ያቀረበለት ጥያቄዎች ያተኮሩት በማን ዙሪያ ላይ እንደነበረ ነው የምታየው? በተለይም ሁለተኛውን የሙሴ ጥያቄና የእግዚአብሄርን መልስ ስንመለከት፤ ለእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሄርን ማንነት ሲጠይቁት መልስ እንዲኖረው ከመሆኑ ባሻገር ለራሱ የሚተርፈው ምን ነገር አግኝቷል ትላለህ?
6. በቁ16-17 ላይ እግዚአብሄር ለሙሴ ወደ ግብጽ ምድር ሄዶ የሚያደርጋቸውን ነገሮች በቅደም ተከተል ሲያስቀምጥለት እናያለን። በእነዚህን ቁጥሮች ላይ ሙሴ እንዲያደርግ የተነገሩትን ነገሮች በቅደም ተከተል በመዘርዘር ተናገር። በቁ18-22 ውስጥ እግዚአብሄር ፕላኑን በሙሉ ጠቅለል በማድረግ ለሙሴ አጠር አድርጎ አስቀምጦለታል። በቁ18 ላይ ሙሴና ሽማግሌዎቹ ወደ ፈርዖን ገብተው እንዲጠይቁት የተነገራቸው ነገር ምን ነበረ?
7. ቁ19-22 ላይ በምናነብበት ጊዜ እግዚአብሄር አምላክ ሙሴና እነዚህ የእስራኤል ሽማግሌዎች ሊጋፈጡት ስላለው ሰው የሚያውቀው አንድ ነገር እንዳለ ይነግራቸዋል፤ ይህ እግዚአብሄር የሚያውቀው አንድ ነገር ምንድነው? እነዚህን ቁጥሮች ስንመለከት እርሱ ከዚህ እንቢተኛ ሰው እጅ በታላቅ ክንዱ እንደሚያወጣቸው ሲናገር እነርሱ ማድረግ ያለባቸውንም ይነግራቸዋል፤ ምንድነው እነርሱ ማድረግ የሚኖርባቸው? ቁ21-22ትን በጥንቃቄ ያልታዘዘ ሰው የሚጎልበት ምን ነገር ያለ ይመስልሃል?
8. በዘፀ 3፡11-2 ላይ ሙሴ ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዲያወጣ እግዚአብሄር ተልዕኮ ሲሰጠው ይሰማው የነበረውን ያለመብቃት ስሜት እንዲያሸንፍ በተሰጠው የማበረታቻ ቃልና፤ በማቴ 28፡19-20 ላይ ደግሞ ለደቀመዛሙርቱ ሰዎችን ከመንፈሳዊ ባርነት እንዲያላቅቁ በተላኩ ጊዜ በተሰጣቸው የማበረታቻ ቃል ምን ተመሳሳይነት ይታይሃል? አንተስ የተቀበልከውን የወንጌል ተልዕኮ ለመወጣት የመንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋራ መሆን ምን ያህል ብርታት ይሰጥሃል? ከሥጋ በላይ የሆነውን የሰዎችን ነፍስ ከሰይጣን ባርነት ነጻ ለማውጣት የወንጌልን አደራ ሲሰጥህ፤ እግዚአብሄር ራሱ ከአንተ ጋራ ሆኖ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ሁሉ እንደሚሰራ እንጂ ሥራው ለአንተ ብቻ እንደተተወ አድርገህ ማሰብ አይኖርብህም።

# ጥናት አራት ዘፀአት 4፡1-31

የጥናት ዓላማ፡- ሙሴ ለሕዝቡ መልስ ለማዘጋጀት በጠየቃቸው ጥያቄዎች ለራሱ ተጠቃሚ እንደሆነ ሁሉ፤ እኛም ቅዱሳንን ለማገልገል ራሳችንን ለማስታጠቅና ለአገልግሎቱ ለማዘጋጀት በእግዚአብሄር ፊት በምናደርገው ዝግጅት ተጠቃሚዎቹ ከምናገለግላቸው ሰዎች ባልተናነሰ ሁኔታ እኛም እንደምንጠቀም ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሙሴም ወደ እስራኤል ልጆች ሄጄ የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ልኮኛል ስላቸው፤ ስሙ ማን ነው? ብለው ቢጠይቁኝ ምን እላቸዋለሁ? አለው…እኔ ያለሁና የምኖር ነኝ፤ ስለዚህም ያለና የሚኖር ልኮኛል ብለህ ንገራቸው አለው።" ዘጸ 3፡13-14

1. ዘጸ 4፡1-31 በአንድነት ይነበብ። ሙሴ በቀደመው ምዕራፍ ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርቦ ከተመለሰለት በኋላ፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን ሲያቀርብ ይታያል። በዘጸ 3፡1 ላይ በማከታተል የጠየቃቸው ሶስቱ ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው? በሳሙ 17፡49 (ዳዊት)፣ በመሳ 15፡15 (ሳምሶን)፣ በዮሐ 6፡9 እና በመሳሰሉት ክፍሎት እግዚአብሄር በሰዎች እጅ ውስጥ በሚገኝ በተናቀ ነገር ሲሰራ ይታያል። በዚህ ክፍል በተለይም በቁ2-5 ውስጥ እግዚአብሄር በተመሳሳይ በትንሽ ነገር ትልቅ ሥራ ሲሰራ የምናየው በምንድነው?
2. ሙሴ ከዚህ አስቀድሞ ለጠየቃቸው የተለያዩ ጥያቄዎች እግዚአብሄር አምላክ ተገቢውን መልስ ከሰጠው በኋላ፤ በቁ10 ላይ ስንመለከት ሙሴ ጥያቄ ሳይሆን ላለመሄድ የሚያስችለውንና በእግዚአብሄር ዘንድ ግን ተቀባይነት የሌለውን ምክንያት ያቀርባል፤ ይህ ያቀረበው ምክንያት ምን የሚል ነበረ? ለሙሴ ጥያቄ የእግዚአብሄርን ምላሽ በቁ11 ላይ ስንመለከት ብዙ ጊዜ ለብዙ ሰዎች ጥያቄ የሚፈጥር አነጋገርን እናገኝበታለን፤ ይህ በሰዎች ዓዕምሮ ጥያቄ ሊፈጥር ይችላል የምትለው ሃሳብ የትኛው ነው?
3. ከቁ12-14 ላይ እግዚአብሄር ሙሴ ለሚያቀርባቸው የተለያዩ ጥያቄዎችና ላለመሄድ የሚያበቁትን ምክንያቶች ሲጨርስ በቁ12 ላይ የገባለት ተጨማሪ የተስፋ ቃል ምን የሚል ነበረ? እነዚህን ሶስት ቁጥሮች ስናነብ ሙሴ ጥያቄውና ምክንያቱ ሁሉ ባለቀበት ጊዜ ሲያቀርብ የምናየው ሃሳብ ምን የሚል ነው? እግዚአብሄርስ ሙሴ ላቀረበለት ሃሳብ ስሜቱ በምን መንገድ ነው የገለጸው?
4. ከቁ3፡11 ጀምሮ ሙሴ እግዚአብሄር የተለያዩ ጥያቄዎችን ሁሉ ሲጠይቀውና ጥርጥር ባሳየበት ወቅት እንኳን ተአምራቶችን በማሳየት እንደመለሰለት እንጂ ሲናደድበት አንመለከትም፤ ታዲያ በዚህ በቁ13 ላይ ሙሴ የተናገረው ነገር ለምን ይመስልሃል የእግዚአብሄርን ቁጣ ያነደደው? ከዚህ ሁኔታ ለራሳችን ህይወት መቅሰምና መማር የምንችለው አንድ እውነት ምንድነው?
5. ቁ14-20 ላይ በተለይም ደግሞ 14-17ትን ስናነብ እግዚአብሄር በሙሴ አነጋገር የተቆጣ ቢሆንም እንኳን እርሱን ጣል አድርጎ ወደ ሌላ ሰው ልቡን ሳይመልስ እንደገና ተጨማሪ ድጋፍ ሲሰጠው እናያለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተገቡለት ምን ተጨማሪ ተስፋዎች ታያለህ? በሙሴ እጅ ለብዙ ዘመናት የነበረችውና አሁን ከእግዚአብሄር ጋራ ጊዜ ባጠፋበት ወቅት ተአምር ያደረገችው የሙሴ በትር ትባል የነበረችው በዚህ ክፍል ውስጥ ስሟ ተቀይሮ እናያለን፤ የተቀየረው ስሟ ምን የሚል ነው?
6. በቁ21-26 ላይ ስናነብ በተለይም በቁ22 ላይ ሙሴ ሄዶ ለፈርዖን ማለት ያለበትን ነገር በአፉ ሲያስቀምጥ እናያለን፣ ይህ እግዚአብሄር ለሙሴ የሚሰጠው መመሪያ ፈርዖን የተደረጉትን ተዓምራቶች ሁሉ አይቶ ለመልቀቅ እንቢ ካለ በኋላ እንደሆነ የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው? እግዚአብሄር ሙሴን ሊገድለው የፈለገበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
7. ቁ27-31 በአንድነት ይነበብ። በቁ14 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር ለሙሴ ወንድሙ አሮን እየመጣ እንደሆነ፣ መጥቶ እንደሚገናኘውና፣ ሲያየውም ደስ እንደሚለው ሲናገር፤ በቁ27 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር አሮንን ወደ ሙሴ እንዲሄድ ሲነግረው እናያለን። ከዚህ ሁኔታ ውስጥ ስለ እግዚአብሄር ምሪት መማር የምንችለው ነገር ምን ይታይሃል?
8. በምዕራፍ 3 ሆነ በምዕራፍ 4 ላይ ሙሴ የጠየቃቸው አብዛኞዎቹ ጥያቄዎች ከህዝቡ ሊመጡ ይችላሉ ብሎ የገመታቸው ናቸው። ለእነርሱ መልስ ለመስጠት ባደረገው ዝግጅት ሙሴ ለራሱ ምን ያህል ተጠቅሟል ብለህ ታምናለህ? ቅዱሳንን ለማገልገል በምታደርገው ዝግጅት አንተ ራስህ ተጠቃሚ እንደምትሆን ምን ያህል ገብቶሃል? የእግዚአብሄርን ቅዱሳን ለማገልገል በእግዚአብሄር ፊት በምናጠፋው ሰዓት ተጠቃሚ የሚሆኑት ተገልጋዮቹ ብቻ ሳይሆኑ እኛም እንደምንጠቀም መረዳት ያስፈልገናል።

# ጥናት አምስት ዘፀአት 5፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- ሙሴ ከእግዚአብሄር ጋራ ለመከራከር ያበቃው ነገር መጀመሪያውኑ የተገባለትን ተስፋ ሙሉ ለሙሉ አለመረዳቱ እንደሆነ ሁሉ፤ እኛም እግዚአብሄር የገባልንን የተስፋ ቃል ምንነት በትክክል መረዳታችን ከስህተት ለመጠበቅ ወሳኝነት እንዳለው ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሙሴም ወደ እግዚአብሄር ተመልሶ፤ አቤቱ ጌታ ሆይ በዚህ ህዝብ ላይ መከራ ያመጣኸው ለምንድነው? የላክኸኝ ለዚሁ ነው?...አንተም ሕዝብህን ከቶ አልታደከውም አለው።" ዘጸ 5፡22-23

1. ዘጸ 5፡1-23 በአንድነት ይነበብ። በዘጸ 4፡31 ላይ ሙሴና አሮን እግዚአብሄር እንደላካቸው የእስራኤልን ሕዝብ ማሳመን እንዳልተቸገሩ እንመለከታለን። በዘጸ 5፡1-2 ላይ ከምናነበው፤ ከግብጽ ንጉሥ ከፈርዖን ጋራ ካካሄዱት ንግግር ስንመለከት እግዚአብሄር የላካቸውን ሃሳብ ሲያስተላልፉ መልዕክታቸው ምን ያህል ተቀባይነት አግኝቷል? በቁ2 ላይ ሙሴና አሮን ሕዝቡን እንዲለቅ እግዚአብሄር እንዳዘዘው ሲነግሩት፤ ፈርዖን ስለ እግዚአብሄር የጠየቀው አንድ ጥያቄ ምን የሚል ነበረ?
2. በቁ1 ላይ ሙሴና አሮን ሕዝቡን እንዲለቅ ለፈርዖን ላቀረቡለት ሃሳብ መልሱን ሲመልስላቸው በቁ2 ላይ ለጠየቃቸው ጥያቄ በቁ3 ላይ በድጋሚ ያንኑ መልዕክት ሲያስተላልፉ የፈርዖንን ጥያቄ በከፊሉም ቢሆን የመለሱት ምን በማለት ነበረ? በቁ2 እና በቁ3 ውስጥ ሙሴና አሮን ለፈርዖን በተደጋጋሚ የእግዚአብሄርን ሕዝብ እንዲለቅ ያቀረቡለትን ጥያቄ በቁ4-5 ላይ ፈርዖን ድርጊታቸውን እንደምን አድርጎ ሲቆጥረው ነው የምናነበው?
3. በቁ6-9 ውስጥ ፈርዖን የእግዚአብሄርን ሕዝቡን ለአምልኮ የመልቀቅ ጥያቄ ከማቃለልና እንቢተኛነቱን ከማሳየት በተጨማሪ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ንጉሱ ሲወስድ የምንመለከተው ተጨማሪ እርምጃ ምንድነው? እነዚህን ቁጥሮች ስንመለከት፤ ሙሴና አሮን ሕዝቡ እግዚአብሄርን ያመልክ ዘንድ ወደ ምድረበዳ ለመሄድ የጠየቁት ጥያቄ በፈርዖን አመለካከት እንደምን ተደርጎ ነው የተወሰደው?
4. በቁ10-14 ላይ ስናነብ ሙሴና አሮን በእግዚአብሄር ትዕዛዝ መጥተው ለፈርዖን እንዲያስተላልፉት የተሰጣቸውን መልዕክት ካስተላለፉ በኋላ ይህ ከእግዚአብሄር የሆነው የነጻነት መልዕክት በእስራኤላውያን ሕይወት ውስጥ ያስከተለው ምን ነገር እንመለከታለን? እነዚህን አምስት ቁጥሮች ስንመለከት እስራኤላውያን በፈርዖን የተጣለባቸውን ጭድ ሳይሰጣቸው የቀድሞውን ያህል ጡብ የመስራት ሃላፊነታቸውን ለመወጣት እንዳልተቻላቸው የሚጠቁመን የትኛው ሃሳብ ነው? አንዳንድ ጊዜ ጠላት የሰዎችን ነጻ መውጣት ስለማይወድ ባለው ሃይሉ ሁሉ ከነጻነት ሊያስቀር እንደሚሞክር መዘንጋት የለብንም።
5. በቁ15-16 ላይ ከምናነበው ሃሳብ በመነሳት፤ ለፈርዖንና ለግብጻውያኑ እስራኤላውያን ባሮቻችን ናቸው ብሎ ማሰቡን ሙሉ ለሙሉ የተቀበሉት ነገር እንደሆነ ስናይ፤ ይህንን አመለካከት የያዙት ግብጻውያኑ ብቻ እንዳልሆኑና እስራኤላውያንም ከዚያ ባልተናነሰ መንገድ ውስጣቸው የገባና ተቀብለው የሚኖሩት ነገር መሆኑን በምን እንረዳለን? በተመለከትናቸው ሁለት ቁጥሮች ውስጥ የእስራኤላውያን ሃላፊዎች ለፈርዖን ያቀረቡት መማጸኛ በቁ19-21 ላይ ያስገኘላቸው ምላሽ ምን ይመስል እንደነበረ ተናገር። እግዚአብሄርን አምላክህን መማጸን ረስተህ ከጠላትህ ጋራ ድርድር ያደረግህበት ጊዜ ይኖር ይሆን?
6. በቁ22-23 ላይ በድፍረት ከእግዚአብሄር የተቀበለውን መልዕክት ወደ ፈርዖን ይዞ ሄዶ የነበረው ሙሴ ከእግዚአብሄር ጋራ ሲነጋገር ይታያል። እነዚህን ሁለት ቁጥሮች ስናነብና እንደ ሙሴ አነጋገር ከሆነ በቀጥተኛ አነጋገር አይበለው እንጂ እንደ እግዚአብሄር ጥፋት ተደርገው በሙሴ አፍ የተነገሩትን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ዘርዝር። የሙሴ ጥያቄዎች መልስ የሚያስፈልጋቸው እንደሆኑ ቢታወቅም እንኳን፤ እግዚአብሄር ግን በዘጸ 6፡1 ላይ ስንመለከት ቀድሞ ከሆነው ነገር ይልቅ ያተኮረው በምን ላይ ሆኖ ነው የምታየው?
7. በዘጸ 3፡19-20 ባለፈው ሙሴ ከእግዚአብሄር ጋራ በነበረው ውይይት ላይ የተነገረውን ሃሳብ ስናነብ፤ በዚህ ክፍል በቁ22 ላይ ደግሞ ሙሴ የሚናገረውን ሃሳብ በፊት ከተናገረው ጋራ ስናነጻጽረው፤ ሙሴ የዘነጋው አንድ ነገር ምን ይመስልሃል? እግዚአብሄርን ከመክሰሳችን በፊት እኛ ራሳችን የተገባልንን ቃል ኪዳን ምንነት በትክክል ለመረዳት መሞከር ከስህተት ያድነናል።

<u>ጥናት ስድስት ዘፀአት 6፡1-30</u>

የጥናት ዓላማ፡- ሊያደርግ ያቀዳቸውን ተዓምራቶች ሁሉ ለሙሴ በቅድሚያ እንዳላስታወቀው ሁሉ፤ አንዳንድ ጊዜ እኛም አንድን ነገር ለማድረግ ስንታዘዝ፤ ልናከናውንለት ከሚያዘን ነገር ባሻገር እኛ በማየት የማንመላለስ ሰዎች ሊያደርገን ስለሚፈልግ ነገሮችን ሁሉ በአንድ ጊዜ ከመግለጽ ይልቅ አንዱን ታዘን ስንጨርስ የሚቀጥለውን ደግሞ ሊገልጥልን እንደሚወድ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…አንተም ህዝብህን ከቶ አልታደግሃቸውም አለው። ከዚያም እግዚአብሄር ሙሴን፤ አሁን በፈርዖን ላይ የማደርገውን ታያለህ፤ ከሃያሉ እጄ የተነሳ እንዲሄዱ ይለቃቸዋል፤ ከሃያሉም እጄ የተነሳ ከሃገሩ ያስወጣቸዋል አለው።" ዘጸ 5፡23-6፡1

1. ዘጸ 6፡1-30 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ስናነብ በፈርዖንና በእግዚአብሄር መሃል ሕዝቡን ከባርነት ነጻ የመልቀቅና ያለመልቀቅ ግብ ግብ ሲካሄድ፤ ከእግዚአብሄር ሃያል እጅ የተነሳ ፈርዖን የሚያደርጋቸውን ነገሮች በሁለት ዓይነት መንገድ ሲገልጽ ይታያል፤ እነዚህ ሁለት የገለጠባቸው መንገዶች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። በቁ2-5 ላይ ስንመለከት ተስፋ የተገባላቸው ሰዎች በሕይወት እንደሌሉ እናውቃለን፤ ታዲያ እግዚአብሄር የእስራኤላውያንን ስቃይ መስማቱ፤ አስቀድሞ ቃል ኪዳን የገባላቸውን ሰዎች እንደሰማ ሆኖ የሚያስቆጥረው ነገር ምንድነው?
2. በቁ6-8 ላይ በሚገኙት ሶስት ቁጥሮች ውስጥ ብቻ ከእስራኤላውያኑ ምንም ነገር እንዲያደርጉ ሳይጠብቅ እግዚአብሄር ለሕዝቡ የሚያደርጋቸውን ለመጥቀስ የተጠቀመባቸው ቢያንስ ስድስት ቃላት እናነባለን፤ እነዚህ ስድስት ቃላት ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በመሃል ላይ የሰፈረና እግዚአብሄር ይኸንን ሁሉ ከማድረጉ የተነሳ የእስራኤል ልጆች የሚደርሱበት አንድ የመደምደሚያ ሃሳብ እንዳለ ቁ7 ይነግረናል፤ ይህ የሚደርሱበት የመደምደሚያ ሃሳብ ምን የሚል ነው?
3. በቁ6-8 ላይ እግዚአብሄር ለሕዝቡ ለእስራኤል ሊያደርግ ያለውን መልካም ነገሮች ሁሉ ለሙሴ ከነገረው በኋላ፤ በቁ9 ላይ ከምናነበው ነገር ሙሴ ከእግዚአብሄር የተቀበለውን መልዕክት ለሕዝቡ ባስተላለፈ ጊዜ የሕዝቡን አቀባበል የሚገጸው አንድ ቃል ምን የሚል ነበረ? ሙሴ ከእግዚአብሄር ተቀብሎ ላስተላለፈው መልዕክት በቁ9 ላይ የምናየው አቀባበላቸው በዘጸ 4፡31 ላይ ከምናየው መሉ በሙሉ የተለየ እንደሆነ እንመለከታለ፤ ሕዝቡን ወደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የከተታቸው ነገር ምን እንደሆነ ነው የምናየው?
4. በቁ9 እና 10 ላይ እግዚአብሄር በሕዝቡ ተስፋ መቁረጥና ሙሴን ለመስማት እንቢ በማለታቸው ላይ እንዳላተኮረ፤ ሆኖ እስራኤልን ተስፋ ባስቆረጠው ነገር ላይ ሲናገር ነው የምናየው። የፈርዖን እንቢተኛነትና የህዝቡ ተስፋ መቁረጥ የእግዚአብሄርን የመጀመሪያ ትዕዛዝ እንዲሻሻል አድርጎታል ወይ? እግዚአብሄር ሊያደርግ ወይም ሊፈጽም የፈለገውን ነገር ሰዎች እንቢ በማለታቸው ምክንያት ሃሳቡን ቀይሮ ሌላ ቀለል ወዳለ ነገር እንደማይቀይረው መረዳት ጠቃሚ ነው።
5. ቁ12 ላይ ስናነብ ሙሴ በድጋሚ ወደ ፈርዖን ፊት ያንኑ መልዕክት ይዞ እንዲሄድ በታዘዘ ጊዜ ለምን መሄድ እንደሌለበት ሲናገር ያቀረባቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን እንደነበሩ ተናገር። ሙሴ ወደ ፈርዖን ላለመሄድ ለእግዚአብሄር ላቀረባቸው ምክንያቶች በዘጸዓት ምዕራፍ ሶስት ውስጥ ገና ተልዕኮውን በሰጠው ሰዓት ለጥያቄዎቹ ሁሉ መልስ እንደሰጠው በዚህ ክፍል ውስጥ መልስ ሲሰጠው ታያለህ ወይ?
6. እስራኤልን ከባርነት ነጻ ለማውጣት የተላኩት ሙሴና አሮን ወንድማማቾች መሆናቸውን በአንድም በሌላም መንገድ ሰምተን ይሆናል፤ የእነዚህ ሁለት ወንድማማቾች አባትና እናት ስም ማን ይባል እንደነበረ ከቁ13-20ን በማንበብ ተናገር። ቁ21-27ትን በማንበብ በዚህ በቁ20 ላይ የተመለከትናቸው ሙሴና አሮን እስራኤልን ነጻ ለማውጣት የተላኩት እነዚህ ራሳቸው እንደሆኑ ማወቅ የሚያስችለን ምን ሃሳብ ትመለከታለህ?
7. በቁ28-30 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር አያውቀው ይመስል ሙሴ ለሶስተኛ ጊዜ የአፉን ኮልታፋነት ለእግዚአብሄር እንደነገረው እርሱም ደግሞ አይዞህ ኮልታፋነትህን እፈውሰዋለሁ የሚል ተስፋ ሳይሰጠው ነው ተልዕኮውን የሰጠው። እግዚአብሄር ኮልታፋነቱን ሳያሻሽልለት እንዳለ ሊጠቀምበት መወሰኑ ለእኛ ምን ዓይነት እውነት ሊያስተምረን ይችላል ትላለህ?
8. በዘጸ 5፡22-23 ውስጥ ሙሴ እግዚአብሄር እንዳለው ሕዝቡን ባለመታደጉ የተሰማውን ስሜት ሲገልጽ፤ በዘጸ 6፡1 ላይ ደግሞ ሌላ ማድረግ ያለበትን ነገር ይነግረዋል። ነገሮችን ለሙሴ ለማቅለል፤ ፈርዖን ከመልቀቁ በፊት ዘጠኝ ተዓምራቶችን አይቶ የሚለቀው በመጨረሻ የበኩር ልጆቻቸው ሲሞቱ እንደሆነ አስቀድሞ መንገር ያልፈለገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? እግዚአብሄር አንድን ነገር እንድናደርግ ሲያዘን፤ የእርሱን ስራ እንድንሰራለት ብቻ ሳይሆን እኛም በእርሱ ላይ መታመንን እንድንለማመድ ስለሚፈልግ ማድረግ የሚኖርብንን ነገሮች ሁሉ በአንድ ጊዜ ግልጽ ላያደርግልን ይችላል።

# ጥናት ሰባት ዘፀአት 7፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- በፈርዖን አለመታዘዝ ምክንያት የሚያስተዳድረው ሕዝብ ዋጋ መክፈሉን እንደቀጠለ ሁሉ፤ እኛ በምናሳየው እንቢተኛነት ምክንያት ሌሎችን የሚጎዳና ዋጋ ሊያስከፍል የሚችል ነገር ውስጥ ልናስገባቸው እንደምንችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ተመልሶ ወደ ቤተ መንግሥቱ ገባ እንጂ ይህንን ከቁም ነገርም አልቆጠረውም። ግብጻውያን ሁሉ የወንዙን ውሃ መጠጣት ባለመቻላቸው ውሃ ለማግኘት የአባይን ዳር ይዘው ጉድጓድ ቆፈሩ።" ዘጸ 7፡23-24

1. ዘጸ 7፡1-25 በአንድነት ይነበብ። ዘጸ 6፡30 ላይ ሙሴ ስለራሱ ያለውን አመለካከት ስንመለከትና በዘጸ 7፡1 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር ስለ ሙሴ የሚያየውን ነገር በማነጻጸር ተናገር። በቁ1-2 ውስጥ የሰፈረውን ሃሳብ ስናይ እግዚአብሄር ሊያደርግ ያሉትን ነገሮች ሊያስተላልፍ ያቀደበትን መንገድ እንመለከታለን። በምን መንገድ ነው እግዚአብሄር ፈቃዱን ከፍጻሜ ለማድረስ የወሰነው?
2. በቁ3 ላይና በሌሎችም የተለያዩ ክፍሎች ከምናነባቸው ጥቅሶች ስንመለከት እግዚአብሄር ራሱ የፈርዖንን ልብ እንዳደነደነ ነው በሚመስል መልኩ ነው ሰፍሮ የምናየው፤ ሆኖም ወደ ዘጸ 3፡19 ላይ መለስ ብለን ስናነብ በዚህ ሃሳብ ላይ ሙሉ በሙሉም ባይሆን እንኳን በከፊሉ ሊረዳን የሚያስችለን ምን ሃሳብ እንደሚታይህ ተናገር። በቁ4 ላይ እግዚአብሄር ገና በባርነት በግብጻውያን ጭቆና ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች በሶስት ዓይነት ስሞች ሲጠራቸው እንመለከታለን፤ እነዚህ ሰስቱ ስሞች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
3. ቀደም ብለን ባጠናነው ጥናት ውስጥ ሙሴና አሮን ወንድማማቾች እንደሆኑ፣ የአባትና የእናታቸው ስም ማን ይባል እንደነበረ ሁሉ ተመልክተናል። ይህ ክፍል በተለይም ቁ5-7 ስለ እነዚህ ወንድማማቾች የሚነግረን ተጨማሪ ምን መረጃ እናገኛለን? እነዚህን ቁጥሮች ስንመለከት እግዚአብሄር አምላክ ሕዝቡን እስራኤልን ከግብጻውያን ባርነት ከማስለቀቅ ባሻገር ሌላ ተጨማሪ ግብ እንደነበረው ያሳዩናል፤ ይህ በዚህ ክፍል የምናነበው አንደኛው እግዚአብሄር ሊያደርግ የፈለገው ነገር ምንድነው?
4. ቀደም ባለው ቁጥር ላይ አሮን የሙሴ ታላቅ ወንድም እንደነበረ ተመልክተናል፤ በቁ8-13 ውስጥ ስንመለከት ደግሞ በፈርዖን ፊት በሚቀርቡበት ወቅት ትዕዛዝን የሚሰጠው ታላቅ ለታናሽ ሳይሆን ታናሽ የሆነው ሙሴ ታላቁ ለሆነው አሮን መሆኑን ስናይ፤ ከዝህ ሁኔታ መማር የምንችለው እውነት ምንድነው? በቁ13 ላይ "...እግዚአብሄር ተናግሮ እንደነበረው አላደመጣቸውም።" የሚል ሃሳብ እናገኛለን። ይህ እንደሚሆን እግዚአብሄር የተናገረው መቼ ነበረ?
5. ቁ14-22 በአንድነት ይነበብ። ይህ ክፍል እግዚአብሄር በፈርዖን ፊት ካደረጋቸው ተአምራቶች አንዱ እንጂ ይህንን ብቻ እንዳላደረገ እናውቃለን። እግዚአብሄር በዚህ ምንባብ መሰረት ፈርዖን ሕዝቡን እንዲለቅና ወደ ምድረበዳ ሄዶ እንዲያመልከው ላደረገው ተአምር የንጉሱ ምላሽ ምን ነበረ? የግብጽ ንጉስ ፈርዖን ይህንን ዓይነት ተዓምር ሲደረግ በአይኑ እየተመለከተ ራሱን ለእግዚአብሄር ከማስገዛት ይልቅ ላለማመን የሚያስችለውን የራሱ የሆነ መንገድ ማዘጋጀቱ ስለ ተአምራት ሊያስተምረን የሚችለው ነገር ምን ታያለህ?
6. እግዚአብሄር ለሚያደርጋቸው እውነተኛ ተአምራቶች ሁሉ የፈርዖንም ጠንቋዮች (ሰይጣንም) የራሱን ተአምር ሲያደርግ ነው በዚህ ክፍል የምናየው። ሰውየው የሚናገረውን ነገር እውነት ይሁን ሃሰት እግዚአብሄር ቃል ከመመርመር ይልቅ ተአምርን ስላዩ ብቻ ሰውየው ከእግዚአብሄር መሆን አለበት ብለው ለሚደመድሙ ሰዎች ይህ ክፍል በምን መንገድ ነው የሚቃወማቸው?
7. ቁ22 ላይ በምናነብ ጊዜ ፈርዖን ይህም ሁሉ ሆኖ ልቡን እንዳደነደነና እግዚአብሄርን መገዳደር እንደቀጠለ እናያለን። በቁ23-25 ላይ ስናነብ በፈርዖን ትዕቢት ዋጋ እየከፈለ ያለው ማን እንደሆነ ነው የምናየው? በአንተ አለመታዘዝ ምክንያት ጓደኞችህ፣ ቤተሰብህ፣ አብረውህ የሚሰሩ ወይም ሌሎችን ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችል ይገባሃል ወይ? እኛ በምናሳየው እንቢተኛነትና ትዕቢት የተሞላበት ምላሽ ሌሎች ዋጋ ሊከፍሉ እንደሚችሉ ማሰብ ይገባናል።

# ጥናት ስምንት ዘፀአት 8፡1-32

የጥናት ዓላማ፡- አስማተኞቹ መቅሰፍትን ማምጣት እንጂ መመለስ ባለመቻላቸው ለመፍትሄ ወደ እግዚአብሄር እንዲጸለይለት መለመኑ፤ እኛ የምናመልከው አምላክ መቅሰፍትን የማምጣት ችሎታ ብቻ ሳይሆን የመጣውንም መቅሰፍት ለማቆምም ጭምር ሥልጣን እንዳለው ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ከዚያም ሙሴ ከፈርዖን ተለይቶ ወደ እግዚአብሄር ጸለየ። እግዚአብሄር ሙሴ የለመነውን አደረገ።” ዘጸ 8፡30

1. ዘጸ 8፡1-32 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ውስጥ በምናየውም ሆነ ሌሎቹንም መቅሰፍቶች በግብጽ ላይ ሲያመጣ ሙሴንንና አሮንን በመጠቀም እንደሆነ ተመልክተናል፤ እግዚአብሄር በራሱ ጓጉንቸሮቹን በዚህና በዚያ ሥፍራ ሄዳችሁ የግብጽን መንደሮች አሽብሩ ማለት ሲችል ለምንድነው እነዚህ ሁለት ሰዎች ያስፈለጉት? የዚህ የጓጉንቸሮቹ መቅሰፍት ከዚህ በፊት ከሆኑት መቅሰፍቶች ሁሉ የተለየ የሚያደርገው ምን ነገር ይታይሃል?
2. አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሄር ህዝቡን ከግብጽ አገር ባርነት ነጻ ለማውጣት አሥር መቅሰፍቶችን ወይም ተአምራቶችን እንዳደረገ ነው የሚነገረው፤ በአንተ አመለካከት እንደ ተአምር መቆጠር የነበረባቸውና ያልተቆጠሩት የትኞቹ ይመስልሃል?
3. ቁ8-11ን ስንመለከት ፈርዖን ሙሴንና አሮንን እንዲጸልዩለት እንደለመናቸውና እነርሱም ደግሞ በጥያቄው መሰረት በመጸለይ ሁኔታው እንዲለወጥ እንዳደረጉ የምናነብ ሲሆን፤ በዚህ ታሪክ ውስጥ ለአንባቢ ሁሉ ጥያቄ ሊፈጥር እንደሚችል የምታስበው አንድ ሃሳብ የትኛው ነው? ሙሴና አሮን የግብጽ ምድር ከጓጉንቸሮቹ ነጻ እንዲሆን መጸለያቸውና፤ በዚህ ድርጊታቸውም ምክንያት መቅሰፍቱ ከአገሪቱ መወገድ በፈርዖንና በሕዝቡ ልብ ውስጥ ሊያመጣ የሚፈለገውን ውጤት ሙሴ ምን በማለት ነው የሚገልጸው?
4. በቁ12-15 ውስጥ ሙሴና አሮን ከጸለዩ በኋላ እግዚአብሄር ጸሎታቸውን ሰምቶ በምድሪቱ ላይ የነበሩት ጓጉንቸሮች ሁሉ እንደሞቱ፤ ሆኖም ፈርዖን ደግሞ ሁኔታው በተቀየረለት ጊዜ እንደገና ለመልቀቅ እንቢ እንዳለ እናነባለን። ሙሴና አሮን የዚህ ዓይነት እንቢታ ከፈርዖን ሲገጥማቸው ይህ የመጀመሪያቸው እንዳልሆነና በተደጋጋሚ የሆነባቸው ሲሆን፤ ለምንድነው እነዚህ ሰዎች በቃ ደጋግመህ ያደረግኸው ነገር ስለሆነ አናምንህም ወዳንተም ተመልሰን አንመጣም ያላሉት?
5. በቁ16-19 ላይ የምናነበው መቅሰፍት ከአሁን በፊት ተደርገው ከነበሩት መቅሰፍቶች ሁሉ የሚለይበት ጥቂት ነገሮች ይታያሉ፤ ይህንን መቅሰፍት ከሌሎቹ መቅሰፍቶች ልዩ የሚያደርጉትን ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ተናገር። ከበፊቱም ጀምሮ የፈርዖን ልብ ደንዳና እንደሆነ በብዙ መንገድ እንደተረጋገጠ እናውቃለህ፤ ሆኖም በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኘውን ሁኔታ ከሌላዎቹ ሁሉ ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
6. በቁ20-23 ላይ ስናይ እግዚአብሄር ፈርዖንን በእንቢተኝነቱ የተነሳ ከመቅጣት ባሻገር ሌላ ሊያስተምረው የፈለገውን እውነት ማየት ይቻላል፤ ይህ ፈርዖን እንዲያውቀው የተፈለገው እውነት ምን ነበረ? ቁ24-27 ላይ ፈርዖን ከእግዚአብሄር ጋራ በጀመረው ትግል በመሸነፍ ላይ መሆኑን የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው?
7. ቁ28-32 ላይ ያለው በአንድነት ይነበብ። አስቀድሞ በቁ25 ላይ ፈርዖን ችግሩ ሲብስበት ህዝቡ በዚያው በግብጽ አገር ሆኖ ለእግዚአብሄር እንዲሰዋ እንደፈቀደ የተመለከትን ሲሆን፤ በቁ28 ላይ ስንመለከት ሙሴ ጠንክሮ የእግዚአብሄርን ቀጥተኛ ትዕዛዝ ለማስፈጸም ባደረገው ቁርጥ ውሳኔ ፈርዖን ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነው ነገር ምን ነበረ? በዚህ ክፍል ውስጥ እስራኤል ሳይርቁ ወጣ ብለው መስዋዕት እንዲሰው ከመፍቀድ ባሻገር የተናገረው ተጨማሪ ነገር ምን እንደነበረ ተናገር።
8. ቁ5-8 የፈርዖን አስማተኞች እነሙሴ ያደረጉት ማድረግ እንደቻሉ። በቁ8 ላይ ፈርዖን ጓጉንቸሮቹን ለማስወገድ ከራሱ ጠንቋዮች ይልቅ ሙሴንና አሮንን መለመኑ ምን ያስተምረናል? አምላክህ እንደሌሎች አማልክት መቅሰፍትን ማምጣት ብቻ ሳይሆን መቅሰፍትንም ማቆም የሚችል አምላክ እንደሆነ ምን ያህል ገብቶሃል? እግዚአብሄር አምላክ መቅሰፍትን ማምጣት ብቻ ሳይሆን የመጣውንም መቅሰፍት ለማቆም ሥልጣን ያለው አምላክ መሆኑን ልንረዳ ያስፈልገናል።

# ጥናት ዘጠኝ ዘፀአት 9፡1-35

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ለፈርዖን በነገው እለት እንዲህና እንዲያ ይሆናል ሲል የጉራ ወይ የፉከራ እንዳልነበረ ሁሉ፤ በእኛም ህይወት ወስጥ ቢሆን እግዚአብሄር አንድን ነገር እንደሚያደርግ በቃሉ ተስፋን ከሰጠን፤ እርሱ ተናገረ ማለት ተፈጸመ እንደ ማለት እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…በነገው ዕለት እግዚአብሄር በምድሪቱ ላይ ይህን ያደርጋል። በማግሥቱም እግዚአብሄር ነገሩን ፈጸመው፤ የግብጻውያን እንስሳት በሙሉ አለቁ፤ ነገር ግን የእስራኤላውያን ከሆኑት እንስሳት አንድም አልሞተም።" ዘጸ 9፡5-6

1. ዘጸ 9፡1-35 በአንድነት ይነበብ። ሙሴና አሮን በእግዚአብሄር ትዕዛዝ ወደ ፈርዖን ከመጡበት ጊዜ አንስቶ መልዕክታቸው በቁ1 ላይም እንደተጻፈው "ያመልኩኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ" የሚል እንደነበረ እናውቃለን። ለምን ይመስልሃል እግዚአብሄር "ሕዝቤን ልቀቅ" ከማለት ለአምልኮ እንደሚፈልጋቸው መናገር ያስፈለገው?
2. ቁ2-7 ውስጥ ስንመለከት ፈርዖን ሕዝቡን መልቀቅ እንደሚኖርበት ያለዚያ ግን እግዚአብሄር ክፉን መቅሰፍት በከብቶቻቸው ላይ እንደሚያመጣ፤ በከብቶቻቸው ላይ በሚመጣው ክፉ መቅሰፍት ግን የእስራኤላውያንን ከብቶች እንደማይነኩ ተናግሮ ያንኑ ሲፈጽመው እናያለን። እግዚአብሄር በእነርሱ ከብቶች ላይ ያደረገውን ካየ በኋላ፤ ለምንድነው ፈርዖን ሰዎችን ልኮ ስለእስራኤላውያን ከብቶች ላይ ደርሶ ወይም አልደረሰ እንደሆነ ለማረጋገጥ የፈለገው? እግዚአብሄር የተናገረው ነገር በትክክል እንደተፈጸመ በራሱ ሰዎች ካረጋገጠ በኋላ እንኳን በእንቢተኛነት መቀጠሉ ስለዚህ ሰው ምን ይነግረናል?
3. ቁ8-14ትን ስናነብ በተለይም ቁ13 እና 14 ምንም እንኳን ፈርዖን ግብጽን ይወክል እንጂ የእግዚአብሄር መቅሰፍቶች በማን ላይ እንደተሰነዘሩ ነው የሚነግረን? እስከ አሁን የተመለከትናቸው አብዛኛዎቹ መቅሰፍቶች የመጡት አሮን በትሩን እንዲዘረጋ ተነግሮት ነበረ፤ በቁ8-14 ትን ስናነብ ግን አሮን ሳይሆን ሙሴ ትብያውን ወደ ሰማይ እንዲበትን ነው የተነገረው። የዚህ ዓይነቱን የእግዚአብሄር አሰራር በመመልከት ለእኛ ሕይወት መማር የምንችለው ነገር ታያለህ?
4. እግዚአብሄር ለፈርዖን በቁ15 ላይ "አሁን እጄን ዘርግቼ አንተንና ህዝብህን ከገጸ ምድር ሊያጠፋችሁ በሚችል መቅሰፍት በመታኋችሁ ነበር።" በማለት ሲናገር ምን ለማለት እንደፈለገ ነው የምትረዳው? እግዚአብሄር ስሙን በዓለም ዙሪያ እንዲታወቅ ሊያደርግ የሚችልባቸው ሁለት መንገዶ አሉ ቢባልና በቁ16ትን ላይ የምንመለከተው አንደኛው ነው ቢባል ሁለተኛ ስሙን ለማስታወቅ የሚጠቀምበት መንገድ ምንድነው ትላለህ? አንተስ በእንቢታህ ወይስ በእሽታህ ለስሙ ማስተዋወቂያ ትሆናለህ?
5. ቁ17-19 ላይ እግዚአብሄር ቀጥሎ በግብጽ ምድር ላይ ሊመጣ ያለውን የበረዶ መቅሰፍት ለፈርዖን ሲነግረው የምንመለከት ሲሆን፤ በዚህ የመቅሰፍት አዋጅ ውስጥ እንኳን የጸጋ ነገር ሲገለጥ ይታያል፤ ይህ በዚህ ቦታ የምታየው የጸጋ መልዕክት የትኛው ነው? በቁ21 እና በቁ22 ውስጥም የእግዚአብሄርን የጸጋ መልዕክት በተለያዩ መንገዶች ያስተናገዱት ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ተናገር።
6. ቁ22-30 እግዚአብሄር እንደተናገረው ከባድ የበረዶ መቅሰፍትን በግብጽ ምድር ላይ ባመጣ ጊዜ ፈርዖን በምድሪቱ ላይ ለደረሰው ነገር ሲሰጥ የምንመለከተው ምላሽ ምን ነበረ? "አሁንም ቢሆን እግዚአብሄር አምላክን እንደማትፈሩ አውቃለሁ።" ሲል፤ ሙሴ የፈርዖንን ልብ የማንበብ ችሎታ የለውም፤ ታዲያ በዚህ ሥፍራ "አውቃለሁ" የሚለውን የተናገረው ከምን ተነስቶ ይመስልሃል?
7. ቁ31-35 ላይ ፈርዖንና ሹማምንቱ የእግዚአብሄር ባሪያ ሙሴ ስለ እነርሱ ቀደም ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የተናገረው ቃል እውነት እንደነበረ ያረጋገጡት በምን መንገድ እንደነበረ ተናገር።
8. ወደ ኋላ መለስ ብለን ቁ5ትንና ቁ6ትን ስናነብ እነዚህ ቁጥሮች ከእግዚአብሄር ባህርያት መሃል አንደኛውን ያጎላሉ ቢባል፤ የሚያጎሉት ባህርይ የትኛውን ነው ትላለህ? በአንተ ህይወት ውስጥ ይህንን የእግዚአብሄር ምን ያህል ግልጽ ሆኖ ታየዋለህ? እግዚአብሄር የተናገረውን ነገር የሚፈጽም አምላክ ስለሆነ፤ እርሱ አንድን ነገር ተናገረ ማለት ልክ ተፈጸመ እንደማለት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

# <u>ጥናት አስር ዘፀአት 12፡1-51</u>

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር አምላካችን ከፊታችን ሊመጣ ያለውን ሁኔታ አስቀድሞ ማየት ስለሚችል፤ በጊዜው ለእኛ ባይታየንም እንኳን የእርሱን ሁሉን አዋቂነት በመተማመን የሚያዘን ትዕዛዛት ለጊዜው ባይገቡንም እንኳን መታዘዛችን ለራሳችን ጥቅም እንደሆነ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ስትበሉም ልብሳችሁን ለብሳችሁ፣ ባጭር ታጥቃችሁ፣ ጫማችሁን አድርጋችሁ፣ በትራችሁን ይዛችሁ፣ በጥድፊያ ብሉት የእግዚአብሄር ፋሲካ ነው።" ቁ11 "ግብጻውያን አገራቸውን በአስቸኳይ ለቀው እንዲወጡላቸው እስራኤላውያንን አጣደፏቸው።" ቁ33

1. ዘጸ 12:1-51 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር የተዓምራቱን ወይም የመቅሰፍቱን መደምደሚያ ለማድረግ ሲነሳ ለሕዝቡ የሰጠውን መመሪያ እናነባለን። በቁ1-3 ውስጥ ስንመለከት ይህ ዛሬ እግዚአብሄር የሚያደርገው ነገር በወደፊቱ የእስራኤል ህይወት ውስጥ ስለሚኖረው ትጽዕኖ የሚናገረው ምን ነገር ታያለህ? ቁ1-6ትን ስናነብ በትዕዛዛቱ መሃል እግዚአብሄር ለህዝቡ የራሳቸውን ውሳኔ እንዲያደርጉ የተወላቸውንና ሊቀይሩ የማይችሏቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ጥቂቶቹን ተናገር።
2. ቁ7-11 ላይ በዚያን ሌሊት የሚታረደውን ጠቦት ምን ማድረግ እንደሚኖርባቸው መመሪያ ይሰጣል። አስቀድመው በመጀመሪያ ደረጃ ጠቦቱን ካረዱት በኋላ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ነገር ምንድነው? እያንዳንዱ ቤተሰብ ያረደውን ጠቦት ስለሚበላበት ሁኔታ ዝርዝር ባለ መንገድ መመሪያ እንደተሰጠ እናነባለን፤ ከእነዚህ መመሪያዎች መሃል ዋነኞች ብለህ ከምታስባቸው መሃል ጥቂቶቹን ነገሮች ተናገር። በቁ1-11 ካነበብነው ውስጥ ለአዲስ ኪዳን ጥላ ሊሆን ይችላል የምትለውን አንድ ሃሳብ ሰንዝር።
3. በአስራ አንዱ ምዕራፎች ውስጥ እግዚአብሄር የፈለገውን አይነት ተዓምር ራሱ በፈለገው ሰዓት በማድረግ ግብጽን ሲቀጣ አይተናል፤ በቁ1-11 ያለውን ክፍልና በቁ12-13 ያሉትን ሃሳቦች ስንመለከት፤ በምዕራፍ 12 ላይ የምናነበውን ተዓምር ከዚህ አስቀድሞ ካደረገበት መንገድ ለየት የሚልበት ምን ነገር ይታይሃል? በቁ14-20 ላይ በሰፈረው ሃሳብ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ ብትባል እንዴት ትገልጸዋለህ? አንተስ እግዚአብሄር በህይወትህ የሰራቸውን ሥራዎች ዘወትር ታስታውሳለህ ወይ?
4. በቁ21 ላይ ከእግዚአብሄር ተቀብሎ ሙሴ ለህዝቡ መመሪያ ሲሰጥ "ቶሎ ሄዳችሁ ለየቤተሰቦቻችሁ የሚሆን ጠቦት መርጣችሁ የፋሲካን በግ እረዱ።" ያለው አነጋገር፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሆነው ነገር የሚለየው በምን መንገድ ነው? ቁ21-23 ትን በምናነብበት ጊዜ የእስራኤል ሰዎች ቤተሰቦቻቸውን በሙሉ ሊመጣ ካለው የሞት መቅሰፍት ለማዳን ከፈለጉ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ከእግዚአብሄር የሰሙት ነገር ምን ነበረ?
5. ዘጸ 5፡1-2 ላይ ፈርዖን ስለ እግዚአብሄር የነበረውን አስተሳሰብ ስንመለከትና፤ በዘጸ 12፡24-32 ያለውን ክፍል በተለይም ደግሞ ቁ31-32ትን ስንመለከት ፈርዖን በእግዚአብሄር ያሳይ ከነበረው ከትዕቢቱና ከአመለካከቱ እንዳወጣው የሚጠቁመን ምን ሃሳብ ትመለከታለህ? በቁ24-28 ውስጥ ፋሲካን አስመልክቶ ወደፊት ምን መሆን ያለባቸውን ነገር ነው የተነገራቸው። ለምን ይመስልሃል እግዚአብሄር በፋሲካ ላይ ልዩ ትኩረትን የሚያደርገው? ፋሲካ የሚለውን ሃሳብ በአንተ ውስጥስ የሚያመጣው ትዝታ ምንድነው?
6. ቁ37-42 ላይ ያለውን ሃሳብ በማንበብ የእስራኤል ህዝብ በግብጽ ምድር የኖረባቸው የዓመታቱ ቁጥር ምን ያህል ነበረ? እግዚአብሄር አምላክ ለአብርሃም ለዘሩ የከነዓንን ምድር እንደሚያወርስ ሲነግረው ይህንን ያህል ዘመን እንደሚወስድ አብርሃም ይጠብቅ ይመስልሃል ወይ? ይህ ሃሳብ ስለ እግዚአብሄር የተስፋ ቃል በአጠቃላይ ምን ያስተምርሃል?
7. በቁ43-51 ውስጥ እግዚአብሄር ለህዝቡ የፋሲካን በዓል አከባበር እንዴት መሆን እንዳለበት ከተናገረው መሃል ለአንተ ጎልቶ የሚታዩህን ሁለት ነገሮች ብቻ በመጥቀስ ተናገር።
8. በቁ33-36 ላይ ግብጻውያን ከአገራቸው እንዲወጡላቸው ያሳዩትን ሁኔታ ስናነብና፤ ወደ ቁ11 ላይ መለስ ብለን ደግሞ እግዚአብሄር የፋሲካውን በግ በምን ሁኔታ ሆነው መብላት እንደሚኖርባቸው የሰጣቸውን ትዕዛዝ ስናይ፤ እግዚአብሄር ይህንን ያህል ህዝቡን ማቻኮል ስለነበረበት ሁኔታ ምን መማር እንችላለን? እግዚአብሄር ሲያዝህ በጊዜው ያልገባህ ቆይቶ ግን አሃ ያልከው ሁኔታ አለወይ? እግዚአብሄር የሚያዘንን ነገሮች ለጊዜው ምን መልካም ነገር ሊወጣባቸው እንደሚችል ባይገቡንም እንኳን እርሱ ለእኛ በጎ ስለሚያስብ በእሽታ መታዘዝ መልካም ነው።

<u>ጥናት አስራ አንድ ዘፀአት 13፡1-22</u>

የጥናት ዓላማ፡- የእስራኤል ሕዝብ ሌሊቱንም ሆነ ቀኑን 24 ሰዓት ሁሉ ጉዞውን መጓዝ እንዲችል እግዚአብሄር በቀን በደመና አምድ፣ ሌሊት ደግሞ በእሳት አምድ ሕዝቡን እንደመራ ሁሉ፤ ሁኔታዎች ብርሃን በሆኑበት ቀናት ብቻ ሳይሆን ቀናቶቹ የጨለሙ በሚመስሉባቸውም ጊዜያት ሁሉ እግዚአብሄር ከእኛ እንደማይለይ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ስለዚህ በቀንም ሆነ በሌሊት መጓዝ ይችሉ ዘንድ… በቀንም ሆነ በሌሊት የደመናውና የእሳቱ ዓምድ ከህዝቡ ፊት የተለየበት ጊዜ አልነበረም።" ዘጸ 13፡21-22

1. ዘጸ 13፡1-22 በአንድነት ይነበብ። እግዚአብሄር የፈርዖንን እንቢተኛነት ለመስበር የግብጽን የበኩር ልጆች በመምታት እንዳወጣቸው እንዲያስታውሱ ለማድረግ ለእስራኤል ሕዝብ እንዲያደርጉት በቁ1-3 ላይ ያዘዛቸው ነገር ምን ነበረ? በቁ3 መጨረሻ ላይ "እርሾ ያለበትን ማንኛውንም ነገር አትብሉ።" የሚለውንና በ1ኛ ቆሮ 5፡7፣ ሉቃ 12፡1 የመሳሰሉትን ክፍሎች ስታነብ፤ እርሾ የሚለው ነገር መጽሐፍ ቅዱሳችን ከምን ጋራ ሲያያይዘው ታያለህ?
2. ቁ4-5 ትን ስናነብ፤ ለአብርሃምና ለዘሩ እንዲወርሱት ሊሰጣቸው ቃል ኪዳን በገባላቸው ምድር ውስጥ ነዋሪ እንደነበሩ በዚህ ክፍል የምንመለከታቸው ሕዝቦች እነማን ናቸው? በዚህ ክፍል ከሙሴ አነጋገር መረዳት የምንችለው እግዚአብሄር ለእነአብርሃም ማርና ወተትን የምታፈሰውን የከንዓንን ምድር እንደሚያወርሳቸው ቃል ሲገባላቸው፤ ምድሪቱን ሊወርሱ ያላቸው ቃል የተገባላቸው እነ አብርሃም ራሳቸው እንዳልነበሩ የሚነግረን ሃሳብ የትኛው ነው?
3. በቁ6-8 ውስጥ ስንመለከት እስራኤላውያን እንዲያከብሩት የተነገራቸውን በዓል ለምን እንደሚያከብሩት እንዲያውቁ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባሻገር እግዚአብሄር የሚጠብቅባቸው ነገር እንደነበረ እንረዳለን፤ ይህ እንዲያደርጉት የሚጠብቅባቸው ነገር ምን ነበረ? አብዛኛውን ጊዜ ከግብጽ ባርነት የመውጣት ነገር በአጠቃላይ የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ እንደሆነ ሲነገር ነው የሚታየው፤ በዚህ ክፍል ይህ የእግዚአብሄር ድርጊት በጋራ ያደረገላቸው ቸርነት ከመሆን አልፎ ለእያንዳንዱ ሰው ግላዊ ነገር መሆኑን የምናየው እንዴት ነው? አንተስ ኢየሱስ ለዓለም ሁሉ የሰራውን የደህንነት ሥራ ለአንተ ለግልህ የተሰራልህ እንደሆነ ተቀብለሃል ወይ?
4. ቁ11 እና ቁ12 ላይ ስናነብ እግዚአብሄርና ሕዝቡ አንዳቸው ለሌላቸው የሚሰጣጡትን ነገር እንመለከታለን። እግዚአብሄር ለህዝቡ የሚሰጣቸው ነገር ምንድነው? ሕዝቡስ ለእግዚአብሄር እንደሚሰጡ የተነገረው ነገር ምንድነው? የዚህ የስጦታ አሰጣጥ ቅደም ተከተል ወይም ቀድሞ የሚሰጠውና የሚከተለው ማን እንደሆነ ተናገር። ወደ እኛ ሕይወት ስንተረጉመውም እግዚአብሄር አስቀድሞ ሕይወትን ስለሰጠን እንጂ፤ ይህ ዓይነቱ ቅደም ተከተል ለእኛ የክርስትና ሕይወት ምን ሊያስተምረን ይችላል ብለህ እንደምታምን በራስህ ቃላት ለማስረዳት ሞክር።
5. ማናችንም ብንሆን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ስንፈልግ አቋራጭ ነው ብለን በምናስበው መንገድ መጠቀም እንደምንፈልግ ይታወቃል፤ በዚህ ቦታ እግዚአብሄር ሕዝቡን ሊመራ የሚችልበት በጣም አጭር የሆነ መንገድ እያለ ረጅሙንና አስቸጋሪ የሆነውን መንገድ የመረጠላቸው ምክንያት ለምን ነበረ? እግዚአብሄር ለእስራኤላውያኑ በየት በኩል መሄድ እንደሚፈልጉ ምርጫን ቢሰጣቸው የትኛውን መንገድ እንደሚመርጡ ትገምታለህ? ከዚህ መማር የምትችለው ነገር ካለ ለወገኖች አካፍል።
6. ቁ20-22 ላይ እግዚአብሄር አምላክ ለሕዝቡ ሲያደርግላቸው የምናየው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር ይህንን ነገር ለእነዚህ ሰዎች ያደረገበት ዋነኛው ምክንያት ምን ነበረ? አንተስ በህይወትህ እግዚአብሄር የዚህ ዓይነት መልካምነቱን የተለማመድክበት ጊዜ ካለ ለወገኖች አካፍል። የክርስትና ህይወታችንን ነገሮች በተመቻቹና ባልተመቻቹባቸው ሁኔታዎች ሁሉ መጓዝ እንድንችል እግዚአብሄር ከእኛ እንደማይለይ ልናውቅ ያስፈልገናል።

# ጥናት አስራ ሁለት ዘፀአት 14፡1-31

የጥናት ዓላማ፡- በግብጻዊያን ወታደሮች ላይ ሲያደርግ እንዳየነው፤ እግዚአብሄር አምላክ ሰዎች ማድረግ የማይችሉትን ነገር ማድረግ እንዲችሉ ማስቻል ብቻ ሳይሆን፤ በነገሩ የተራቀቁበትንና በደንብ የሚያውቁበትን ነገር እንኳን ማድረግ እንዳይችሉ የማድረግ ችሎታ እንዳለው ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "መንዳት እንዳይችሉም የሰረገላዎቹን መሽከርከሪያዎች አቆላለፈባቸው፤ ግብጻውያኑም ከእስራኤላውያን እንሽሽ! እግዚአብሄር ግብጻውያንን እየተዋጋላቸው ነው አሉ።" ዘጸ 14፡25

1. ዘጸ 14፡1-31 በአንድነት ይነበብ። እግዚአብሄር ጠላቶቻቸውን በባህር ውስጥ እንዲከድንላቸው ካስፈለገ እስራኤላውያን በቁ1-2 ውስጥ ተደጋግሞ የተነገራቸውን አንድ ትዕዛዝ መከተል ወሳኝ እንደነበረ እናውቃለን፤ ይህ መከተል የነበረባቸው ትዕዛዝ ምንድነው? ቁ1-4 ስንመለከት እግዚአብሄር የእስራኤል ጠላት የሆነውንና ሕዝቡን ሊያጠፋ በሙሉ ሃይሉ የመጣውን የፈርዖንንና ሰራዊቱ እስከ መጨረሻው ለመደምሰስ የወሰዳቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ዝግጅቶች ምን እንደሚመስሉ ተናገር።
2. ከቁ5-9 እግዚአብሄር እስራኤላውያንን እንዲያሳድድ የፈርዖንን ልብ እንዳደነደነ አንብበናል፤ ይህ የፈርዖን የልብ መደንደን ለእስራኤል ልጆች የእግዚአብሄርን ማዳን ከማየታቸው በፊት ምን ተሰምቷቸዋል ብለህ ታስባለህ? ሁሉ ነገር እግዚአብሄር ባቀደው መንገድ ከሄደና ሁኔታዎች ሁሉ ከተቀየሩ በኋላስ የተሰማቸው ስሜት ምን ይመስልሃል? አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሄር ወዳዘጋጀልን በረከት እንድናልፍና ጠላታችንን ደግሞ ፈጽሞ ድል እንዲሆን ካስፈለገ ለጊዜው ጠላት ያሸነፈ መስሎ እንዲታይ እግዚአብሄር ሊፈቅድ ይችላል። ከፊሊ 1፡28 ጋራ እንዴት እንደሚመሳሰል ተናገር።
3. ቁ10-12 ላይ እስራኤላውያኑ የፈርዖንን ሰራዊት መምጣት በተመለከቱ ጊዜ ያደረጓቸው ሁለት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑና፤ የትኛውም ድርጊታቸው የእምነት ድርጊት እንዳልነበረ ግልጽ የሚያደርግልን ሃሳብ የትኛው ነው? እነዚህ ሰዎች በቁ12 ላይ ሁለት ነገሮችን በማነጻጸር ሲናገሩ እንመለከታለን፤ እነዚህ የሚያነጻጽሯቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? አንተስ ሁኔታዎች በከበዱብህ ቁጥር ወደኋላ የመመለስና ነጻነትህን ጥለህ በባርነት መኖር እንደሚሻል ልብህ ይከጅልብሃል ወይ?
4. ቁ13-18 ላይ እግዚአብሄር ለሕዝቡ እንዲዋጋላቸውና ዛሬ የሚያዩአቸውን ግብጻውያን ነገ እንዳያዩአቸው ካስፈለገ፤ እስራኤላውያን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው የተነገሯቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናችው? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር በራሱ ባህሩን መክፈልም ሆነ ወደ ሥፍራው እንዲመለስ ማድረግ ሲችል ለምን ይመስልሃል ሙሴ በትሩን እንዲዘረጋ በማዘዝ ተዓምራቱን ለማድረግ የፈለገው?
5. በቁ19-20 ሲሆን በምናነበው ታሪክ ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር አምላክ ሕዝቡን እስራኤልን ከጠላቶቻቸው ጥቃት ለመከላከል ሲወስድ የሚታየው እርምጃ ምንድነው? ይህንን ዓይነቱን እግዚአብሄር ለህዝቡ ለመቆም ያደረገውን ድርጊት ስትመለከት፤ ከዚህ ሁኔታ ለህይወታችን ልንማረው የምንችለው ምን ነገር ይታይሃል?
6. በቁ28 ላይ የምንመለከተው ሁኔታ ሙሴ በቁ13 እና 14 ላይ የተናገረውን ንግግር እውነተኛነት የሚያረጋግጠው በምን መንገድ ነው ብለህ ታምናለህ?
7. በቁ31 ከምናነበው ሃሳብ በመነሳት፤ በዚህ ምዕራፍ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሄር በግብጻውያን ላይ ያደረገውና ለሕዝቡ ሲያደርግ ያየናቸው ነገሮች ሁሉ ያመጡት ዋጋ ወይም ውጤቱ ምን ነበረ
8. እንደሚታወቀው የግብጽ ወታደሮች በጦርነትና በሰረገላ አጠቃቀም የሰለጠኑ ናቸው፤ ታዲያ በቁ25 ላይ ተመልሰን ስንመለከት ሰረገላዎቻቸውን በትክክል መጠቀም የተቸገሩበት ምክንያት ለምንድነው? በኢሳ 54፡17 ላይ እንደተነገረው ጠላት ሊያጠፋህ አዘጋጅቶት የነበረ መሳሪያ ከሸፎ አይተህ ታውቃለህ ወይ? ጠላታችን በተራቀቀበትና ችሎታ አለኝ የሚለውን ነገር ይዞ ቢመጣብንም እንኳን፤ እግዚአብሄር አምላካችን ያንንም የማከሸፍ ችሎታ እንዳለው ልንረዳ ያስፈልገናል።

# ጥናት አስራ ሶስት ዘፀአት 15፡1-27

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር የእስራኤል ሕዝብ በእርሱ መታመንን እንዲማሩ ውሃ በሌለበት ምድረበዳ እንዲያልፉ እንደፈቀደ ሁሉ፤ ዛሬም ቢሆን እኛን በእርሱ ላይ ያለንን እምነት ለማጠንከር ሲል በምድረበዳ ውስጥ እንድናልፍ ሊፈቅድ እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ለሶስት ቀናት ውሃ ሳያገኙ በምድረበዳ ተጓዙ…ከዚያም አስራ ሁለት ምንጮችና ሰባ የዘንባባ ዛፎች ወዳሉበት ወደ ኤሊም መጡ።” ዘጸ 15፡22፣ 27

1. ዘጸ 15፡1-27 በአንድነት ይነበብ። በምዕራፍ 14 መጨረሻ ላይ እግዚአብሄር ሕዝቡን ለመታደግ ሲል በግብጻዊያን ላይ ያደረገውን ተዓምራት የተመለከቱት እስራኤላውያን እግዚአብሄርን እንደፈሩና፣ እንዳመኑበትም የመጨረሻው ቁጥር ይነግረናል። የቁ15ትን አጀማመር ስትመለከት፤ የእግዚአብሄር ፍርሃት በሕዝቡ ልብ ውስጥ ምን ሲፈጥር ነው የሚታየው? ይህ የሕዝቡ ድርጊት ዳዊት በመዝሙሩ 22፡23 ላይ “እናንተ እግዚአብሄርን የምትፈሩ አወድሱት” ካለው ሃሳብ ጋራ ምን ያህል ተመሳሳይነት ታይበታለህ?
2. ሙሴና የእስራኤል ልጆች እግዚአብሄርን ለማመስገን እንደ ምክንያት አድርገው የጠቀሷቸውን ከ1-3 በሚገኙት ቁጥሮች ላይ ብቻ ከተነገሩት መሃል አንተ የምታያቸውን በመዘርዘር ተናገር። ቁ4 እና በቁ5 ውስጥ ደግሞ በግብጻዊያን ላይ የእግዚአብሄር እጅ የሰራቸውን ነገሮች ይነግረናል፤ እነዚህ ጸሐፊው የሚዘረዝራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. በቁ9 ላይ ስናነብ በእግዚአብሄር ሕዝብ ላይ የተነሳው የእስራኤል ጠላት ምኞቱና ፍላጎቱ ምን እንደነበረ ነው የሚነግረን? ይህንን ሁሉ የጉራና የማን አለብኝነት ንግግር የሰማው እግዚአብሄር በቁ10 ላይ ምን ዓይነት እርምጃ ሲወስድ ነው የምንመለከተው? ጠላትህ ሊያጠፋህ ከበስተኋላህ የሚዝተውንና የሚያቅደውን ደባ እግዚአብሄር ተንኮሉን ለማክሸፍ ተግቶ እንደሚሰራ ምን ያህል ታስተውላለህ?
4. ጸሐፊው እግዚአብሄር አምላክን ከአማልክት ጋራ በማወዳደር በቁ11 ላይ ሲናገር እናየዋለን። እንድ ጸሐፊው አነጋገር፤ እግዚአብሄርን ከአማልክት ከሚለዩት ነገሮች መሃል ሶስቱን ብቻ ይጠቅሳል፤ በዚህ ቁጥር ላይ የሚጠቀሳቸው እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
5. በቁ13-15 ላይ የእግዚአብሄር ለሕዝቡ በሚያደርገው ድንቅ ነገር በአካባቢያቸው የሚገኙት የተለያዩ መንግሥታት የሚሰማቸው ስሜት ምን እንደሚሆን እናነባለን። በዚህ ቦታ የተዘረዘሩትን የአምስቱን አገራት ሥሜት ምን እንደሆነ ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የአካባቢውን ነገሥታት እንደሚያስደነግጡ የተነገረላቸውና እግዚአብሄር ለህዝቡ እንደሚያደርጋቸው የተነገሩት ሁለቱ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
6. በቁ16 ላይ የምናነበው እውነት በኢያሱ 2፡10 ላይ ረአብ የኢያሪኮን ከተማ ሊሰልሉ ለመጡት ሰላዮች ከተናገረችው ሃሳብ ጋራ ስታነጻጽር ምን የምትረዳው ነገር አለ? በቁ17 ላይ እግዚአብሄር ህዝቡን አምጥቶ እንደሚተክላቸው ስለተነገረበት ስፍራ በሶስት የተለያዩ መንገዶች ተገልጾ ይታያል፤ እነኚህ ሶስቱ ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
7. የእስራኤል ልጆች በቁ22-24 ላይ እያሳዩ ያሉት የማጉረምረም ባህርይ፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለይም በቁ11 ላይ ስለ እግዚአብሄር ማንነት ከተናገሩት ንግግር ጋራ የማይጣጣም ነው ማለት የሚያስችለን ምን ሃሳብ ይታይሃል? ያ ሁሉ ድንቅ የሆነው ዝማሬና ያማረ አምልኮ እንደዚህ በአጭር ጊዜ ከህይወታቸው ተረስቶ ዛሬ በማጉረምረም መሞላታቸው ለእኛ ምን ዓይነት ትምህርት አለው ብለህ ታምናለህ?
8. በቁ22 ትና በቁ27ት ላይ የሰፈሩትን ሃሳቦች ስናይ፤ ሕዝቡ እግዚአብሄር በሁለት ተቃራኒ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሕዝቡ እንዲያልፉ እንደፈቀደ እናያለን። እነዚህ ሁለት ተቃራኒ ሁኔታዎች ምንና ምንድናቸው? ሕዝቡን በምድረበዳ ውስጥ እንዲያልፉ ለምን የፈቀደ ይመስልሃል? የምታልፍበት አስቸጋሪ ሁኔታ የዚህ ዓይነቱን ጥያቄ ፈጥሮብህ ያውቃል ወይ? የልጆቹ እምነት ዘወትር በእርሱ ላይ የጸናና የተመሰረተ እንዲሆን ስለሚፈልግ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲያልፉ ሊፈቅድ እንደሚችል መዘንጋት አይኖርብንም።

# ጥናት አስራ አራት ዘፀአት 16፡1-36

የጥናት ዓላማ፡- ለእስራኤል ህዝብ በምድረበዳ ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን ምግብ ሳያጓድልባቸው ያዘለቃቸው እግዚአብሄር፤ ዛሬም ቢሆን ለእኛ ለልጆቹ ለዛሬ የታመነልን እግዚአብሄር ነገስ እንዴት እሆናለሁ በሚለው ፍርሃት ውስጥ መኖር እንደማያስፈልገን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሆኖም አንዳንዶቹ በሰባተኛው ቀን ለመሰብሰብ ወጡ፤ ነገር ግን ምንም አላገኙም። ከዚያም እግዚአብሄር ሙሴን አለው፤ ትዕዛዞቼንና መመሪያዎቼን ለመፈጸም እስከመቼ እንቢ ትላላችሁ?" ዘጸ 16፡27-28

1. ዘጸ 16፡1-36 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-3ትን ስናነብ በሙሴና በአሮን ላይ ያጉረመረሙትን የሰዎች ብዛት ሲናገር ጸሐፊው ምን በማለት ነው የሚገልጸው? ይህንን ሳነብ በአዕምሮዬ የመጣው አንድ ጥያቄ፤ ኢያሱና ካሌብም በዚህ ማጉረምረም ተሳትፈው ይሆን እንዴ ብዬ ራሴን ጠየቅሁ፤ አንተስ ኢያሱና ካሌብ በዚህ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ይመስልሃል ወይ? በዚህ ሥፍራ እነዚህ ሰዎች ግብጽን እንደምን አድርገው ሲስሉ ነው የምናነበው?
2. እስራኤላውያኑ ከግብጽ ምድር አወጣጣቸው ሁኔታ ቁ3 እና ቁ6 የተለያዩ ሁለት አስተሳሰቦችን ያንጸባርቃሉ። እነዚህ ሁለት ዓይነት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። "መላው ማህበር በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ።" በማለት ቁ2 ሲናገር፤ በቁ7 ላይ ደግሞ "በእርሱ ላይ ያሰማችሁትን ማጉረምረም ሰምቷልና" ይለናል። ታዲያ ሕዝቡ ያጉረመረሙት ሙሴና አሮን ላይ ሆኖ ሳለ ለምንድነው በእግዚአብሄር ላይ እንዳጉረመረሙ ሆኖ በቁ7 ላይ የተነገረው?
3. በቁ1-12 ውስጥ ቢያንስ ለሰባት ጊዜ በተደጋጋሚ ሲጠቀስ የምናየው ቃል አለ፤ ይህ የሚደጋገመው ቃል ምን የሚል ነው? በቁ7፣ 8፣ 9 እና 12 ላይ ደግሞ ከዚሁ ቃል ጋራ በመያያዝ እንደተነገረ የምናየው ቃል ምን የሚል ነው? አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሄር ጸሎትን የሚሰማና ጆሮዎቹ ለልመናዎቻችን የተከፈቱ እንደሆኑ ሲነገር እንደሰማን አልጠራጠርም፤ ይህ ክፍል በአንጻሩ ሊያስገነዝበን የሚችለው እውነት ምንድነው ትላለህ? ማጉረምረምህም የጸሎትህን ያህል ከእግዚአብሄር ጆሮ እንደሚደርስ ማስታወስ ያስፈልግሃል።
4. ቁ13-16ትን ስናነብ ለእስራኤላውያን የሚያስፈልጋቸውን ምግብ እንዳገኙ የሚታይ ሲሆን፤ ከሰማይ የወረደውን መና አስመልክቶ ደግሞ እነዚህ ክፍሎች የእግዚአብሄር ድርሻና የሕዝቡ ድርሻ ምን እንደነበረ ግልጽ ሆኖ ሰፍሯል። የእግዚአብሄርና የሕዝቡ ድርሻ ምን ምን እንደነበረ ተናገር። በቁ19 ላይ ሙሴ ለህዝቡ ሲሰጣቸው የምናየው መመሪያ በምን መንገድ ነው ጌታ የሱስ ካስተማረን ጸሎት ጋራ ተመሳሳይነት የምታይበት?
5. በቁ 20 ላይ "በማግስቱም ጠዋት ተልቶ መሸተት ጀመረ" የሚል ስናነብ፤ በቁ 24 ላይ ደግሞ "እስከ ጠዋት ድረስ አቆዩት፤ አልሸተተም ወይም አልተላም" ይላል። ያው አንድ አይነት መና አንዴ ሲሸትና ሲተላ፤ በሌላ ቀን ደግሞ ያለመሽተቱና ያለመትላቱ ምክንያቱ ለምንድነው?
6. ቁ 31-36ትን በማንበብ፤ እግዚአብሄር የእሥራኤልን ልጆች በምድረበዳ መናን የመገባቸው ለምን ያህል ጊዜ ነበረ? እግዚአብሄር ሕዝቡን መናው መመገብ ያቆመው ወደ መኖሪያ ምድራቸው ሲደርሱ፣ ወይም ደግሞ ወደ ከነዓን ድንበር ሲደርሱ እንደነበረ ይነግረናል። ለምን ይመስልሃል ያንን ሁሉ ዘመን ሲመግባቸው ቆይቶ ድንበር ላይ ሲደርሱ መናውን ያቆመባቸው?
7. በቁ20 እና በቁ27 ላይ በምንመለከታቸው "ሆኖም አንዳንዶቹ" በመባል የተጠቀሱት ሰዎች ህይወት ላይ የሚታየው ዋነኛ ችግር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ለዛሬ የሚበቃህን በረከት ከእግዚአብሄር ተቀብለህ ለነገህ የሚሆነውን ደግሞ ለማግኘት የራስህን መንገድ የተከተልክበት ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ? ለዛሬ የታመነው እግዚአብሄር ለነገም የሚታመን አምላክ እንደሆነ ማስታወስ ተገቢ ነው።

# ጥናት አስራ አምስት ዘፀአት 17፡1-16

የጥናት ዓላማ፡- ምንም እንኳን ሙሴ ተግቶ በመጸለይና ኢያሱም በትጋት በመዋጋት የድሉን ባንዲራ ለእግዚአብሄር እንዳውለበለቡ ሁሉ፤ በእኛም ሕይወት ለሚገኘው ማናቸውም ዓይነት ድልና በጎ ነገር ሁሉ የእግዚአብሄር ስም ከፍ ብሎ የሚታይበት ሊሆን እንደሚገባ ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- *"ሙሴም መሰዊያውን ሰርቶ እግዚአብሄር አርማዬ ነው ብሎ ሰየመው።"* ዘጸ 17፡15

1. ዘጸ 17፡1-16 በአንድነት ይነበብ። ምዕራፍ 16፡1-3 ትን እና ምዕራፍ 17፡1 ትን ስንመለከት የህዝቡ ችግር በተለያየ ጊዜ የተለያየ ችግር እንደነበረ ነው የምናየው። የምዕራፍ 16 እና የምዕራፍ 17 ውስጥ የህዝቡ ችግሮች ሆነው የተገኙት ነገሮች ምን እንደነበሩ ተናገር። በምዕራፍ 16 ላይ ለረሃባቸው ምክንያት ያደረጉት ማንን ነበረ? በምዕራፍ 17 ላይስ እነዚሁ ሰዎች ለጥማታቸው ተጠያቂ ሲያደርጉ የሚታዩት ማንን ነው?
2. በቁ1-2 የሰፈረውን ሃሳብ በማንበብ እስራኤላውያኑ የተጓዙበት መንገድ ሁሉ የእግዚአብሄር ፈቃድ እንደነበረበት ሊያስረዳን የሚችለው ሃሳብ የትኛው እንደሆነ አስረዳ። የእስራኤልን ልጆች ጉዞ ስንመለከት ከተጓዙባቸው ጎዳናዎች መሃል ብዙ የማይመቹና አስቸጋሪ እንደነበሩ ረሃብና ጥማታቸውን ብቻ ማየት ይቻላል። እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሄር ፈቃድ ጉዟቸውን እየተጓዙ እያሉ እነዚህን በመሳሰሉ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፋቸው ለእኛ መንፈሳዊ ጉዞ ምን ሊያስተምረን ይችላል ብለህ ታምናለህ?
3. የእስራኤል ልጆችን በዘጸ 16፡3፣ 17፡3 እና በመሳሰሉት ክፍሎች ስንመለከት አንድ ችግር በመጣባቸው ቁጥር የሚናገሩት አንድ ተመሳሳይ ሃሳብ እንዳለ እንረዳለን። በተቸገሩ ቁጥር ለመናገር የሚቀናቸው አንድ ነገር ምን ይታይሃል? እነዚህ በቁ3-4 ውስጥ የሰፈረውን ሃሳብ ስናነብ፤ ሙሴ ከህዝቡ ለተነሳበት የማጉረምረም ችግር ከሁሉ አስቀድሞ ሲወስድ የሚታየው የመፍትሄ እርምጃ ምን ማድረግ ነው?
4. በበቁ5-7 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር ሙሴን የቀደመችውን በትሩን ይዞ እንዲወጣ ትዕዛዝ ሲሰጠው እንመለከታለን። ከዚህ ቀደም ብዙ የተለያዩ ተአምራቶች የተሰራባት በትር ዛሬም ደግሞ እንደቀድሞው ይህ በትር እስካለ ድረስ የህዝቡ ችግር መፍትሄ ያገኛል በሚል አመለካከት ሙሴ እንዳይሳሳት ለማድረግ፤ በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ከተናገራቸው ነገሮች ውስጥ ምን ይታይሃል?
5. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እግዚአብሄር ህዝቡን ለምን ተጠማችሁ በሚል አላዘነባቸውም፣ ምክንያቱም ጥማት እግዚአብሄር ራሱ በሰዎች ህይወት ውስጥ የፈጠረው ስሜት ነው። ታዲያ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስትመለከት እግዚአብሄርን ያሳዘነውና ያስቆጣው ነገር ምንድነው ብለህ ትላለህ?
6. ሙሴ ወደ እግዚአብሄር በርትቶ ከጸለየና ድሉን የሚሰጠው እግዚአብሄር እስከሆነ ድረስ ኢያሱ ለምን መዋጋት ያስፈልገዋል? ቁ11 ላይ *"ሙሴ እጆቹን ወደላይ በሚያነሳበት ጊዜ ሁሉ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር፤ እጆቹን ባወረደ ጊዜ ግን አማሌቃውያን ያሸንፉ ነበር።"* ይላል። የሙሴ መጸለይና አለመጸለይ የምን ያህል ሰዎች ህይወት የሚመካበት ነው ትላለህ? በአንተ እጅህን ወደ እግዚአብሄር ማንሳትና አልማንሳት የብዙዎች ሰዎች የመዳን ወይም የመጥፋት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ተረድተሃል ወይ?
7. በዚህ በቁ14 ላይ እግዚአብሄር ይህንን በዚህ ሥፍራ ላይ ለህዝቡ ለእስራኤል ያደረገውን ነገር ኢያሱ መስማቱን ሙሴ እንዲያረጋግጥ ሲነግረው እንመለከታለን። እግዚአብሄር ለሙሴ የተናገረውን ነገር ኢያሱ እንዲሰማ የፈለገበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
8. በቁ15 ላይ *"ሙሴም መሰዊያውን ሰርቶ፣ እግዚአብሄር አርማዬ ነው ብሎ ሰየመው።"* በማለት ይናገራል። ሙሴ እጁ እስኪደክም ጸልዮ፣ ኢያሱ እስኪያልበው ተዋግቶ እያለ ለምን ይመስልሃል ሙሴ ይህንን መሰዊያ እግዚአብሄር አርማዬ ወይም ሰንደቅ ዓላማዬ በማለት የሰየመው? አንተስ ድል ባገኘህና በተሳካልህ ጊዜ የምታውለበልበው ሰንደቅ ዓላማ የማንን ይሆን? በህይወትህ በምታገኘው ማናቸውም ድል የሚውለበለበውና ከፍ የሚለው ስም የእግዚአብሄር እንዲሆን ተጠንቀቅ።

# ጥናት አስራ ስድስት ዘፀአት 18፡1-27

የጥናት ዓላማ፡- ዮቶር እውነቱን ከመፍትሄው ጋራ በመንገር፣ ሙሴም የተነገረውን እውነት በመስማት በትህትና ሥራ ላይ እንዳዋለ ሁሉ፤ እኛም ወገኖች በተሳሳተ ጎዳና ሲሄዱ ስናይ ግንኙነታችንን ለማቆየት ብቻ ብለን እውነቱን ከመናገር ወደኋላ እንዳንል፤ በአንጻሩ ደግሞ ከስህተታችን ለመመለስና እውነቱን ለመንገር ወደ እኛ የሚመጡትንም ወገኖች በትህትና የመቀበል ጸጋ ማዳበር እንደሚገባን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የሙሴ አማት መልሶ እንዲህ አለው። የምትሰራው መልካም አይደለም… ሙሴ አማቱን ሰማ፤ ያለውንም ሁሉ ፈጸመ።" ዘጸ 18፡17፣ 24

1. ዘጸ 18፡1-27 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ ስናነብ፤ የምድያም ካህንና፣ የሙሴ አማት የሆነው ዮቶር ሙሴና እስራኤላውያን ወደሰፈሩበት ምድረበዳ እንደመጣ እናያለን። ይህንን ጉዞ እንዲጀምር ምክንያት የሆነው ነገር ምን ነበረ? ይህንን አይነት ዜና ለዮቶር ይዞለት የመጣው ሰው ማን ነው? አንተስ እግዚአብሄር ለህዝቡ ያደረገውን በጎ ነገርና፤ ከአንተስ አንደበት የሚወጣው ነገር የእግዚአብሄርን ድንቅ ስራ መናገር ወይስ የሰዎችን ልብ የሚጥልና ተስፋ የሚያስቆርጥ ወሬ?
2. ቁ2-7 ላይ ስንመለከት የሙሴ አማት የሆነው ዮቶር እግዚአብሄር ለህዝቡ ለእስራኤል ያደረገውን በጎ ነገር ሰምቶ ሙሴ ወዳለበት ሲሄድ አብሮ የወሰዳቸው ሰዎች እነማን እንደነበሩ በመዘርዘር ተናገር። እነዚህን ስድስት ቁጥሮች ብቻ በማንበብ የዚህ ህዝብ ሁሉ መሪና አለቃ የሆነው ሰው አማቱ ስለሆነው ሰው ስለ ዮቶር ስለነበረው አመለካከት የሚጠቁመን ነገር ምንድነው?
3. በቁ8-12 ውስጥ በምናነብበት ጊዜ ዮቶር ከመምጣቱ ቀደም ብሎ ሰምቶት የነበረውን ነገር ሙሴ በድጋሚ ሲነግረው እንመለከታለን። ሙሴ ለአማቱ ለዮቶር የነገረው አዲስ ነገር ማለትም አስቀድሞ ያልሰማው ብለህ የምትለው ሃሳብ ካለ ተናገር። እግዚአብሄር ለሕዝቡ ያደረገውን ድንቅና ተዓምራት መስማቱ በዮቶር ሕይወት ውስጥ ያስከተለው የአመለካከት ለውጥ እንደነበረ ራሱ ከሚናገረው ንግግር መረዳት ይቻላል፤ ይህ በህይወቱ የሆነው ለውጥ ምን ነበረ? እግዚአብሄር በህይወትህ የሰራውን ነገር መናገር በሌሎች ህይወት ውስጥ መሰረታዊ ለውጥን ሊያመጣ እንደሚችል ማስብ ይኖርብሃል።
4. ዮቶር፣ ሙሴ፣ አሮንና የእስራኤል ሽማግሌዎች በእግዚአብሄር ፊት መልካም ጊዜ እንዳሳለፉ ቁ12 ተናግሮ፤ በቁ13-15 ላይ ሲመጣ ግን የሙሴ አሰራር ለአማቹ ጥያቄ እንደፈጠረበት ይነግረናል፤ የሙሴ አሰራር በዮቶር ላይ የፈጠረበት ጥያቄ ምን ነበረ? ቁ15ትንና ቁ16 ስንመለከት ሙሴ የዮቶርን ጥያቄ ለመመለስ በተናገረው ንግግር ውስጥ እንደምንረዳው፤ ህዝቡ ወደ ሙሴ የሚመጡባቸውን ቢያንስ ሁለት  ምክንያቶች እንደነበሩ እንመለከታለን፤ እነዚህ ምክንያቶች ምንና ምን ነበሩ?
5. ቁ17-18 ስናነብ ሙሴ ሁሉን ነገር እርሱ በማድረጉና የሥራ ክፍፍል ባለመፍጠሩ እየተጎዱ ያሉ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ አማቱ ይነግረዋል፤ እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን ናቸው?
6. ቁ19-22 ውስጥ ዮቶር ለሙሴ ተጨማሪ ሊረዱት የሚችሉትን ሰዎች እንዲመርጥና እንዲሾች ሲነግረው፤ ለዚህ ሥራ እንዲሾማቸው የነገረው ሰዎች ቢያንስ ሶስት መመዘኛዎችን ሊያሟሉ ይገባል፤ እነዚህ መመዘኛዎች ምን ምን ናቸው? ከእነዚህ ቁጥሮች እንደምንረዳው፤ አብዛኛውን ሥራ ለሾማቸው ሰዎች ከሰጠ በኋላ በዮቶር አነጋገር የሙሴ ሃላፊነት ምን እንደሚሆን ነው የሚመከረው?
7. በቁ23 አነጋገር ሙሴ አማቱ የመከረውን ነገር በሥራ ቢተረጉመው ሊሆን የሚችለውን ነገር ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል። ይህንን ምክር መስማቱ የሚያስገኘው መልካም ነገር ምን ይሆናል? ዮቶር የሙሴን ስህተት መናገር ብቻ ሳይሆን መፍትሄ የሚሆነውንም ሃሳብ በፍቅር መንገሩ ለግንኙነታቸው ጸንቶ መቆየት ምክንያት ሆኗል፤ በቁ24-27 ውስጥ ይህንን ሃሳብ የሚደግፍ ምን ምልክት ታያለህ?
8. በዚህ ታሪክ ውስጥ የተመለከትናቸውን ሁለት ሰዎች ማለትም ሙሴንና አማቱን ዮቶርን በሁለቱ መሃል ከተካሄደው ነገር አኳያ ትልቅ ሰዎች ናቸው ሊያሰኛቸው የሚችል ምን ዓይነት ነገር ትመለከታለህ? አንተስ ግንኙነት እንዳይበላሽ እውነትን ከመናገር ወደኋላ ትላለህ ወይ? እንደ ክርስቶስ ተከታዮች እውነትን በፍቅር በመናገር ሰዎችን ከተሳሳተ መንገዳቸው መመለስ፤ እንዲሁም ሌሎች እውነትን በመናገር ከስህተታችን ሊመልሱን ሲሞክሩ በትህትና ማስተናገድ ብልህነት ነው።

# <u>ጥናት አስራ ሰባት ዘፀአት 19፡1-25</u>

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ወደሚገኝበት ተራራ መቅረብ በራስ ላይ የሞት ፍርድ እንደ መፍረድ የነበረውን ሁኔታ ቀይሮ፤ በሞቱ ወደ እግዚአብሄር ፊት በድፍረት እንድንገባ በሩን የከፈተልንን መድሐኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወትር ልናመሰግነው እንደሚገባን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ወደ እግዚአብሄር ቅረቡ፤ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል።" ያዕ 4፡8

"በተራራው ዙሪያ ለህዝቡ ወሰን አበጅተህ ወደ ተራራው እንዳትወጡ…ማንም ተራራውን ቢነካ በእርግጥ ይሞታል።" ዘጸ 19፡12

1. ዘጸ 19፡1-25 በአንድነት ይነበብ። እግዚአብሄር በመሪያቸው በሙሴ እጅ ለእስራኤላውያን አሥርቱን ትዕዛዛት የሰጠበት ሥፍራ ላይ እንደደረሱና ይህም ሥፍራ የሲና ተራራ እንደነበረ ይታወቃል። እስራኤላውያን የሚመሩበት ህግ ሳይኖራቸው የተጓዙበት ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ በትንሹ ስንት ጊዜ ይሆናል ትላለህ?
2. በቁ3-4 ላይ እግዚአብሄር አምላክ በባሪያው በሙሴ በኩል ለእስራኤል ሲናገር፤ ሕዝቡ የስሚ ስሚ ሳይሆን ራሳቸው በአይናቸው የተመለከቱትና የሚያውቁት ነገር አድርጎ የሚነግራቸው ሁለት ነገሮች እናያለን፤ እነዚህ ሁለት የሚነግራቸው ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ይህ እግዚአብሄር አደረኩላችሁ ብሎ ከሚዘረዝራቸው ነገሮች መሃል በተለይም በንስር ክንፍ እንደተሸከማቸው መናገሩ በህይወታቸው የትኛው ጊዜ ላይ ያደረገውን ነገር ሊያስታውሳቸው ፈልጎ ነው ትላለህ?
3. በቁ4-5 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር በባርነት እያሉና ገና የራሱ ህዝብ ሳያደርጋቸው እንዲታዘዙለት ሳይጠይቅ፤ ከባርነት ሕይወት ውስጥ ካወጣቸውና ከቀደመው አለቃቸው ካላቀቃቸው በኋል ከእነርሱ መታዘዝን መጠየቁን ስንመለከት፤ ከዚህ ሁኔታ ውስጥ ለእኛ ሕይወት ልንማረው የምንችለው ምን እውነት ትመለከታለህ?
4. ከቁ5-8 የሰፈረውን ሃሳብ ስናነብ እስራኤላውያኑ በወደፊት ሕይወታቸው ውስጥ ደግሞ ሊያደርግላቸው ያለውን ነገር ሲነግራቸው እናያለን። ቀድሞ አደረግሁላችሁ ላለው ነገር ያልጠበቀባቸው ነገር ግን በዚህ ሥፍራ አሁን አደርግላችኋለሁ ለሚላቸው ነገር ቅድመ ሁኔታ አድርጎ የሚያቀርብላቸው ነገር ምንድነው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስታይ በእግዚአብሄርና በእስራኤል ህዝብ መሃል ከዚህ በኋላ ሊኖር ስላለው ግንኙነት የምታያቸውን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ተናገር።
5. በቁ7 እና በቁ8 ላይ ሙሴ እያደረገ ያለውን ነገር ስንመለከት ሙሴን ካህን ሊያሰኘው የሚያስችል ምን ነገር ትመለከታለህ? በቁ10 እና በቁ11 ላይ ህዝቡ እግዚአብሄርን ለመገናኘት ማድረግ ስለሚኖርባቸው ዝግጅት ለሙሴ ሲነግረው እንመለከታለን። ዛሬስ በዚህ ዘመን እግዚአብሄርን ለመገናኘት መደረግ አለበት የምትለው ዝግጅት አለ ወይ? አለ ብለህ የምታምን ከሆነስ ይህ ዝግጅት ምን ዓይነት መሆን እንደሚኖርበት ለማስረዳት ሞክር።
6. ቁ12-25 በእርጋታ በአንድነት ይነበብ። በዚህ ምንባብ ውስጥ የምናያቸውን ሰዎች ሁሉ ወደ እግዚአብሄር ተራራ መቅረብን አስመልክቶ ቢያንስ በአራት ልንከፍላቸው እንችላለን፤ እነዚህ አራት አከፋፈሎች ምንና ምንድናቸው? ዛሬ እኛ በምንኖርበት ዘመን ውስጥ እግዚአብሄርን መቅረብ በተመለከተአማኞችን በስንት መከፈል ይቻላል ትላለህ?
7. ከቁ12 ጀምሮ ምዕራፉ እስከሚያልቅ ድረስ ህዝቡ ወደ እግዚአብሄር መቅረብ እንደማይችልና ሌሎችም መቅረብ የሚችሉበት ሁኔታ ምን እንደሚሆን የተዘረዘረ ሲሆን፤ ይህንን የተላለፈ ግን እንደሚሞት በግልጽ ተነግሯል። ይህን ሃሳብና በያዕ 4፡8 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ በማነጻጸር ስታነብ ምን እውነት ታያለህ? አንተስ "ወደ እግዚአብሄር አትቅረቡ" በሚለውና "ወደ እግዚአብሄር ቅረቡ" የሚለው ሃሳብ ተገርመህ ታውቃለህ ወይ? ወደ እግዚአብሄር ዙፋን በድፍረት የመቅረባችን ነገር ምን ጊዜም ሊያስገርመን የሚገባ እውነት ሊሆን ይገባል።

# ጥናት አስራ ስምንት ዘፀአት 20፡1-26

የጥናት ዓላማ፡- ሕዝቡን እስራኤልን ከፈርዖን እጅ ከባርነት ነጻ አውጥቶ ለእርሱ እንዲኖሩ እንደጠየቃቸው ሁሉ፤ እኛንም በክርስቶስ ሞት ከሃጥያት ባርነት ነጻ ካወጣን በኋላ ተመልሰን በሃጥያት እንድንጨመላለቅ ሳይሆን፤ ለሐጥያት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር መሆኑን ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እግዚአብሄር እነዚህን ቃሎች ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፤ ከግብጽ ከባርነት ምድር ያወጣሁህ እግዚአብሄር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ።" ዘጸ 20፡1-3

1. ዘጸ 20፡1-26 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናነበው ነገር እግዚአብሄር በባሪያው በሙሴ አማካኝነት አሥርቱ ትዕዛዛት በመባል የሚታወቁትን ለእስራኤላውያን ያስተላለፈበትን ሁኔታ ነው። በቁ1-17 ላይ የሰፈሩትን ትዕዛዛት በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፤ እነዚህ ሁለት መንገዶች ምንና ምን ሊሆኑ ይችላሉ ትላለህ?
2. በቁ4-6 ውስጥ ስናነብ እግዚአብሄር እንደሚቀጣቸውና በሌላ በኩል ደግሞ ፍቅርን የሚያሳያቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ እንመለከታለን። እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ተናገር። እነዚህን ሁለቱን ዓይነት ሰዎች አስመልክቶ የቁጣውንና የፍቅሩን መጠን ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን አነጋገሮች አነጻጽረን ስንመለከት ምን ሊያስረዳን የሚችለው ነገር ይታይሃል?
3. በቁ7 ላይ የምናነበውን "የእግዚአብሄር የአምላክህን ስም ያለ አግባብ አታንሳ" የሚለውን ትዕዛዝ፤ ሮሜ 2፡21-24፣ በ1ኛ ጢሞ 6፡1 እና እነዚህን የሚመስሉትን ጥቅሶች ስንመለከት፤ ይህ ትዕዛዝ ሊሰበርባቸው ከሚችሉት የተለያዩ ሁኔታዎች መሃል እነዚህ ጥቅሶች ጥቅሶች የሚያሳዩን ይህ አንድ መንገድ ምንድነው ማለት እንችላለን?
4. በዘፍ 20፡8 አራተኛውን ትዕዛዝ ስድስት ቀን ተሰርቶ በሰባተኛው ቀን ግን ምንም ዓይነት ሥራ መስራት እንደማይኖርባቸው ያዛል። ስለ በአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ስለ ሰንበት የተሰጠውን ትዕዛዝ በዕብ 4፡9-10 እና ቆላ 2፡16-17 ጋራ በማጣመር ስትመለከተው፤ ዛሬ ለእኛ በዚህ ዘመን ለምንገኝ የአዲስ ኪዳን አማኞች፤ በሳምንቱ ውስጥ ካሉት ቀናት ቅዳሜን ወይም እሁድን ማረፍ ነው ወይስ ሌላ ትርጉም አለው ብለህ ታምናለህ? አማኝ በሰንበት ማረፍ አለበት ብለህ ታምናለህ ወይ? ከሆነስ ምን ዓይነት እረፍት?
5. አምስተኛውና በቁ12 ላይ የተሰጠው አባትንና እናትን ስለማክበር የተነገረውን ትዕዛዝ፤ በኤፌሶን መልዕክት ምዕራፍ 6 ቁጥር 2-3 ውስጥ ጳውሎስ ይህ ትዕዛዝ ከሌሎቹ የሚለይበትን አንድ ነገር ይናገራል፤ ይህ አንድ ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው? በቁ13 ላይ ደግሞ ስድስተኛውን ትዕዛዝ "አትግደል" በማለት ትዕዛዝ እንደተሰጠ እናያለን፤ ታዲያ ይህ አትግደል የሚለው ትዕዛዝ ሐዋርያው ዮሐንስ በመልዕክቱ ውስጥ 1ኛ ዮሐ 3፡15 እኔ ማንንም ገድዬ አላውቅም ለምንል የሚነግረን እውነት ምንድነው? አንተስ እንደ ዮሐንስ አነጋገር ሰው ገድለህ ታውቃለህ ወይ?
6. ቁ18-21ትን ስናነብ ሕዝቡ ከመፍራታቸውና ከመደንገጣቸው የተነሳ ከአሁን በኋላ እግዚአብሄር እንዳይናገራቸው ነገር ግን በሙሴ በኩል እንዲናገራቸው እንደሚፈልጉ ለሙሴ ሲነግሩት እንሰማለን። ይህንን የህዝቡን ጥያቄ ሲሰማ ሙሴ ከእስራኤላውያን ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ ምን ነበረ? እግዚአብሄር ሕዝቡ በሚፈራበት መንገድ የተናገረበትን እውነተኛውን ምክንያት ስንመለከት ልንማር የምንችለው አንድ እውነት ምንድነው?
7. በቁ22-26 ውስጥ ከአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ተደግመው ሲነገሩ የምታየቸው ትዕዛዝ የትኛዎቹ ትዕዛዛት እንደሆኑ ተናገር።
8. በቁ2 ላይ ከፈርዖን ባርነት ነጻ ያወጣቸው እርሱ እግዚአብሄር እንደሆነ ይነግራቸውና፤ ከቁ3 ጀምሮ ደግሞ ነጻ ለወጡት ሰዎች የራሱ የሆነ ትዕዛዛትን ሲያስተላልፍ እንመለከታለን። ይህ የእስራኤል ሁኔታ ሮሜ 7፡18 "ከሃጥያት ነጻ ወጥታችሁ፤ የጽድቅ ባሪያዎች ሆናችኋል።" ከሚለው ከእኛ ሁኔታ ጋራ እንዴት ሊነጻጸር ይችላል ትላለህ? ከባርነት ነጻ መውጣትህ ለሌላ ባርነት እንደሆነ ገብቶሃል ወይ? ከአንድ ባርነት ወደሌላ ባርነት፤ ይኸውም ከሃጥያት ባርነት ለጽድቅ ባርነት እንደተጠራን መርሳት አይገባንም።

# ጥናት አስራ ዘጠኝ ዘፀአት 23:1-33

የጥናት ዓላማ፦ የእስራኤላውያን ጠላቶች ከእነርሱ ጋራ እንዲቆዩ እንደፈቀደ ሁሉ፤ አንዳንዴ በእኛም ህይወት እግዚአብሄር የሚያስቸግሩንንና በቶሎ ከእኛ እንዲያስወገዱልን የምንለምናቸውን ሁኔታዎች ከእኛ ጋራ እንዲቆዩ የሚያደርግበት ምክንያት ለራሳችን ጥቅም አስቦልን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ "ነገር ግን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አላወጣቸውም፣ ምክንያቱም ምድሪቱ ባድማ ሆና የዱር አራዊት ይበዙባችኋል። ቁጥርህ ጨምሮ ምድሪቱን ለመውረስ እስክትበቃ ድረስ ጥቂት በጥቂት ከፊታችሁ አባርራቸዋለሁ።" ዘጸ 23፡29-30

1. ዘጸ 23፡1-33 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ውስጥ ራሳቸውን የቻሉ ቢያንስ አምስቱን ማድረግ የማይገባቸውን ነገሮች ለእስራኤላውያኑ ተሰጥቶ እናነባለን፤ እንዚህ አምስቱ ሕግጋት ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። እነዚህን ትዕዛዛት ትኩረት ሰጥተህ ስትመለከታቸው፤ እኛ በምንኖርበት ዘመን ውስጥ በአንተ አመለካከት ለአማኞች ከእነዚህ ህግጋት መሃል አብዛኛውን ጊዜ ፈተና ሆኖ ሲገኝ የሚገጥምህ የትኛውን ሕግ ነው? ለምን?
2. በቁ4 እና 5 ላይ ሰፍሮ የምናነበው ነገር ከአዲስ ኪዳን ትምህርትና ሃሳብ ጋራ ይሄዳል ብለህ ታምናለህ ወይ? ከሆነስ ይህንን ሃሳብህን ለመደገፍ የሚያስችልህ ጥቅስ ከአዲስ ኪዳን ውስጥ ቢያንስ አንዱን በመጥቀስ ለማስረዳት ሞክር። "በዳኝነት ጊዜ በድሃው ላይ ፍርድ አታጓድልበት" የሚለውን በቁ6 ላይ የተሰጠውን ትዕዛዝ፤ በቁ1-6 ውስጥ ለዚህ ትዕዛዝ ሚዛናዊነት እንዲሰጥ ሆኖ የተነገረው ሌላ ትዕዛዝ ምንድነው ትላለህ?
3. በቁ8ና ቁ9 ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር አታድርጉ ለሚላቸው ሁለት ነገሮች የሰጣቸው ምክንያቶች ምንድናቸው? በተለይም ስለጉቦ በዚህ ቁጥር ላይ ከተናገረው ነገር ልንረዳ እንደምንችለው፤ ጉቦ ማንኛቸውንም ሰው ሊያስት የሚችል ነገር እንደሆነና እኔን አይነካኝም ሊል የሚችል ሰው ሁሉ ሊጠነቀቅ እንደሚገባው ሊጠቁመን የሚችለው ሃሳብ የትኛው ነው? ጉቦን ላለመቀበል ምሳሌ አድርጎ በዘዳ 10፡17 ላይ የሚያሳየን ማንን ነው? አንተስ በዚህ ነገር ላይ መጠንቀቅ እንደሚኖርብህ ምን ያህል ታምናለህ?
4. የጉቦ ነገር ከተነሳ፤ በአገራችን ጉዳይን ለመፈጸም ጉቦን መቀበልና ጉቦን መስጠት የተለመደ ነገር እንደሆነ ግልጽ ነው፤ ታዲያ ይህ የአገራችን ሁኔታ በክርስትና ላይ ወይም በአማኞች ህይወት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተጽዕኖ ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ጉቦን መቀበል ትክክል እንዳልሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ክፍሎችን ጠቅሶ መናገር ይቻላል፤ ጉቦን መስጠትስ ትክክል አይደለም ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ ከእግዚአብሄር ቃል ላይ በመደገፍ ለማስረዳት ሞክር።
5. ቁ10-13ትን ስናነብ ሌሎቹን ትዕዛዛት ሲሰጥ ምክንያቱን እንደእንገራቸው ሁሉ በነዚህም ቁጥሮች ውስጥ ለተሰጡት ትዕዛዛትም ምክንያት ሲሰጥ እናያለን። በሰባተኛው ዓመት ምድሪቱን ማሳረፍና፤ ስድስት ቀን ሰርቶ በሰባተኛው ማረፍ የሚያስፈልገው ለምንድነው? እነዚህን እግዚአብሄር ለእስራኤላውያኑ መሬታቸውን እንዲያሳርፉና ራሳቸውም በሰባተኛው ቀን እንዲያርፉ የሰጣቸውን ምክንያቶች ስትመለከት ስለ እግዚአብሄር ባህርይ ምን ትማራለህ?
6. እረፍትና ለእስራኤላውበቁ14-19 ውስጥ እስራኤላውያን እንዲያከብሯቸው የተነገራቸው ሶስት በዓላት ምን ምንድናቸው? በቁ20-22 አነጋገር መሰረት እግዚአብሄር ለእስራኤል ጠላቶቻች ጠላት እንደሚሆንና፤ የሚቃወሟቸውን ደግሞ እንደሚቃወም እርግጠኞች እርግጠኞች መሆን የሚችሉት መቼ ነው?
7. በቁ23-28 ውስጥ በጣም ብዙ የሆኑ የተስፋ ቃሎችን የገባላቸው ሲሆን፤ በእነዚያ ቁጥሮች ውስጥ ከእስራኤላውያን እንደሚጠበቅባቸው የተነገራቸው ነገር ምን ታያለህ?
8. ቁ29 እና 30 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር የእስራኤልን ጠላት ከመካከላቸው እንደሚያጠፋላቸው፤ ሆኖም ግን ሁሉንም በአንድ ጊዜ እንደማያጠፋቸው ይነግራቸዋል። ጠላቶቻቸውን ሁሉ በአንድ ጊዜ እንደማያጠፋላቸው የሰጣቸው ምክንያት ምን የሚል ነበረ? አንተስ በቶሎ እንዲያስወግድልህ እግዚአብሄርን የለመንከው ነገር ከጠበቅኸው በላይ ጊዜ ወስዶብህ ያውቃል ወይ? በፍጥነት እንዲሆንልን የለመነው ነገር በቶሎ አለመመለሱ ምናልባት እግዚአብሄር ያየው የተሻለ ነገር ሊኖር እንደሚችል ማሰብ ይጠቅማል።

# <u>ጥናት ሃያ ዘፀአት 32:1-35</u>

የጥናት ዓላማ፡- ሙሴ እግዚአብሄር ለአባቶቻቸው የገባውን የቃል ኪዳን በማሳሰብ ልመናውን እንዳቀረበ ሁሉ፤ እኛም በእግዚአብሄር የተስፋ ቃል ማለትም በቃሉ ላይ በመመርኮዝ ድፍረት በተሞላው መልኩ ልመናችንን ወደ ዙፋኑ የማምጣት ድፍረት ሊኖረን እንደሚችል ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ለባሪያዎችህ ለአብርሃም፣ ለይስሃቅና፣ ለእስራኤል፣ ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ፤ ለዘርህም ተስፋ አድርጌ የሰጠኋቸውን ይህችን ምድር ሁሉ እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘለዓለም ርስት ትሆናለች፤ በማለት በራስህ የማልከውን አስታውስ። ዘጸ 32፡13

1. ዘጸ 32:1-35 በአንድነት ይነበብ። ቁ1ድን ስናነብ እስራኤላውያኑ እግዚአብሄርን ረስተው ጣዖትን ለማምለክ እንዲችሉ አሮንን እንዲሰራላቸው ሊጠይቁት ያነሳሷቸው ሁለት ምክንያቶችን እንደነበሩ ክፍሉ ይጠቁመናል፤ እነዚህ ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን እንደነበሩ ተናገር። ሙሴ ረዘም ላለ ጊዜ ከእግዚአብሄር ጋራ ለመቆየት በሄደበት ወቅት ለአሮንና ለሆር የመሪነትን ሃላፊነት እንደሰጣቸው ከዘጸ 24፡14 መረዳት እንችላለን። ቁ1 እና 2ትን ስታይ አሮንን የመሪነት ሃላፊነቱን በሚገባ አልተወጣም ሊያሰኘን ምን ነገር ይታይሃል?
2. የሰው ልጅ ወርቅህን አውልቀህ ስጥ ሲባል በቀላሉ አውልቆ መስጠት እንደማይፈልግ እናውቃለን፤ በቁ1-5 ላይ ስንመለከት ግን ሕዝቡ ሁሉ ያደረጋችሁትን ወርቅ አውልቃችሁ አምጡ ሲባሉ በቀላሉ አውልቀው ለመስጠት ያልተቸገሩት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? እስራኤላውያኑ አሮንን የጠየቁትና እርሱም ደግሞ ለጥያቄአቸው መልስ አድርጎ የሰራላቸውን ነገር ስትመለከት፤ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሄር አምላክ በዘጸ 20 ውስጥ ከሰጣቸው አስርቱ ትዕዛዛት መሃል የትኛውን ነው ጥሰው የተገኙት?
3. እግዚአብሄር በቁ7 ላይ “ከግብጽ ያወጣኻቸው ሕዝብህ” በማለት ሲናገር፤ በቁ11 ደግሞ “ከግብጽ ባወጣኸው ህዝብህ ላይ” በማለት ሙሴ ከእግዚአብሄር ጋራ ሲነጋገር እናነባለን። ታዲያ ይህ ሕዝብ የሙሴ ነው የእግዚአብሄር? ከግብጽ ያወጣውስ ሙሴ ነው ወይስ እግዚአብሄር?
4. ቁ15-18ትን ስንመለከት ሙሴና ኢያሱ ከተራራው ወርደው ሕዝቡ ወደነበሩበት ሰፈር ከመድረሳቸው በፊት ይሰማ ስለነበረው ድምጽ ኢያሱ በሰነዘረው ሃሳብና ሙሴ በሰጠው አስተያየት መካከል የነበረው ልዩነት ምን ይመስል እንደነበረ ተናገር። ይህንን በህዝቡ ዘንድ ይሰማ የነበረውን ድምጽ ከኢያሱ ይልቅ ሙሴ ምንነቱን ለይቶ ለማወቅ የተሻለ እድል ነበረው ማለት የሚያስችለንን ነገር ከምዕራፉ ውስጥ ምን ማየት እንችላለን?
5. ቁ19-24ትን ስናነብ ሙሴ በተመለከተው ሁኔታ እጅግ በተቆጣ ጊዜ ሲወስድ የሚታየው እርምጃዎች ምን ምንድናቸው? በዚህ እግዚአብሄርን ብቻ ሳይሆን ሙሴንም ጭምር እጅግ ባስቆጣው ድርጊት ላይ በቀዳሚነት ተጠያቂ ያደረገው ማንን ነው?
6. በዘጸ 17:2-4 ላይ ሕዝቡ ሙሴን እርሱ ማድረግ የማይችለውን ነገር እንዲሰጣቸው ሊጠይቁት የወሰደውን እርምጃ ስንመለከትና፤ በዚህ ክፍል በቁ23-24 ላይ አሮን እንዲያደርግ የጠየቁትን ነገር ያስተናገደበትን መንገድ ስታነጻጽር በመሪ ላይ መታየት ስለሚኖርበት በህርይ ምን ያስተምረናል?
7. ማቴ 10:37 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን መከተል ማለት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለተከታዮቹ በሚያስተምርበት ወቅት የተናገረው ትምህርት በዚህ ክፍል በቁ25-29 ላይ ከምናነበው ሃሳብ ጋራ በምን መንገድ ሊመሳሰል እንደሚችል አስረዳ። ቁ25-29 ላይ ሙሴን ከህዝቡ ጋራ ስንመለከተውና፤ በቁ30-35 ላይ ላይ ደግሞ በእግዚአብሄር ፊት ቀርቦ ስለሚመራው ህዝብ እያደረገ ያለውን ነገር ስናይ ስለሙሴ ባህርይ የምንረዳው ነገር ምንድነው?
8. በቁ11-14 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት ሙሴ እግዚአብሄር ሕዝቡን እንዲምር ሲለምን እናያለን። እግዚአብሄር ለመማጸኑ በዋነኛነት ሲጠቀምበት የሚታየው አንድ መሳሪያው ምንድነው ትላለህ? አንተስ እግዚአብሄር እንዲሰማህ በፊቱ ይዘህ ለምትቀርበው ነገር እርሱ የሰጠውን የተስፋ ቃል የመጠቀም ልምድን አዳብረህ ይሆን ወይ? በ1ኛ ዮሐ 5፡14 ላይ እንደተነገረው፤ እግዚአብሄር የገባውን የተስፋ ቃል ይዘን ወደ እርሱ መምጣት ሙሉ ድፍረት ኖሮን ለመለመን ያስችለናል።

# ጥናት ሃያ አንድ ዘፀአት 33፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- ያለ እግዚአብሄር መውጣት በሙሴ አመለካከት የማይታሰብ ነገር እንደሆነ ሁሉ፤ ለእኛም በተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ያለ እግዚአብሄር ከመኖር ይልቅ፤ በማይመችና ነገሮች አስቸጋሪ በሆኑበት ሁኔታ ውስጥ ከእግዚአብሄር ጋራ መኖር የሚመረጥ እንደሆነ ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ከዚያም ሙሴ እንዲህ አለው፤ ህልዎትህ ከእኛ ጋራ ካልሄደ ከዚህ አትስደደን።" ዘጸ 33፡15

1. ዘጸ 33፡1-23 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ ከምናነበው ነገርና የቃላት አጠቃቀሙ ስንመለከት፣ እግዚአብሄር ሕዝቡ ባደረጉት ነገርና በሆነው ሁኔታ በዚህ ሰዓት እየተሰማው ስላለው ስሜት ምን መረዳት እንችላለን? በእነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ ስናነብ እግዚአብሄር በወሰደው እርምጃ ሕዝቡ ደግሞ የተሰማቸው ስሜት ምን እንደሚመስል ይነግረናል። የእግዚአብሄርን ውሳኔ አስመልክቶ የሕዝቡ ስሜት መገለጫዎች ሆነው የምናያቸውን ቢያንስ ሁለት ነገሮች ምን ምን እንደነበሩ ተናገር።
2. ቁ1-4ትን ስናነብ እግዚአብሄር ለአባቶቻቸው ለእነ አብርሃም፣ ለይስሃቅና ለያዕቆብ ወደማለላቸው ወተትና ማር ወደምታፈሰው ምድር እንደሚያስገባቸው፤ እንዲሁም በመንገዳቸውና በአገሪቱ ውስጥ የሚኖሩትን ጠላቶቻቸውንም ሁሉ እንደሚያስወጣላቸው ሲነግራቸው እናነባለን፤ ታዲያ ይህ ሁሉ ነገር ከተደረገላቸው የሕዝቡ ሐዘን ከምን የመነጨ ነው ትላለህ? የአንተንስ ልብ ደስ የሚያሰኘው የምትፈልጋቸውን ነገሮች እግዚአብሄር ማሟላቱ ነው ወይስ እግዚአብሄር ራሱን ትፈልገዋለህ?
3. በዘጸ 32፡2 ላይ በአሮን፣ እና በዘጸ 33፡5-6 ውስጥ ደግሞ በእግዚአብሄር አማካኝነት ሕዝቡ ጌጦቻቸውን እንዲያወጡ እንደተጠየቁ እንመለከታለን። በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ውስጥ ጌጦቻቸውን እንዲያወልቁ በተጠየቁባቸው ምክንያቶች መሃል ምን ልዩነት ትመለከታለህ?
4. በቁ7-11 ውስጥ ስንመለከት ሰዎች እግዚአብሄርን መጠየቅና ማነጋገር ሲፈልጉ ሊሄዱ የሚችሉበት ሥፍራ እንደተዘጋጀላቸው እናነባለን። ይህ እግዚአብሄርን ማግኘት የሚቻልበት ሥፍራ የተዘጋጀው የት እንደነበረ ነው የምናየው? ከእግዚአብሄር ጋራ የመገናኛና የመነጋገሪያው ሥፍራ እዚያው ሕዝቡ ሁሉ በሚገኝበትና ግርግር በበዛበት መሃል ሳይሆን ወጣ ብሎ መተከሉን ስንመለከት፤ ሁኔታውን ዛሬ ከእኛ ሕይወት ጋራ ለማዛመድ ቢፈለግ ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል አስረዳ።
5. በቁ12 እና በቁ13 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር ሙሴን "አንተን በስም አውቅሃለሁ፤ በፊቴም ሞገስ አግኝተሃል" እንዳለውና ሙሴ በዚህ አባባል ብቻ ረክቶ እንዳላቆመ ማየት እንችላለን። ሙሴ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄርን ሲጠይቀው የምናየው ነገር ምንድነው? ሙሴ በተራራ ላይ ፊቱ እስከሚያበራ ድረስ ከእግዚአብሄር ጋራ ጊዜ ያሳለፈ፣ ሰው ከጓደኛው ጋራ እንደሚነጋገር ከእግዚአብሄር ጋራ የሚነጋገር እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፤ በዚህ ክፍል አንተን ማወቅ እፈልጋለሁ ሲል ምን ማለቱ ይመስልሃል?
6. በቁ15-16 ከምናነበው ሃሳብ በመነሳት፤ በሙሴ አመለካከት የእግዚአብሄር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን ከሌሎች ህዝቦች የተለዩ እንደሆኑ ያመነበት እንደሆነ እናያለን፤ በዚህ ክፍል መሰረት የእግዚአብሄርን ህዝብ ከሌሎች ሕዝቦች የተለየ የሚያደርገው ዋነኛው ነገር ምንድነው?
7. ወደ ኋላ መለስ ብለን ቁ15ትን ስንመለከት ሙሴ በጊዜው የነበሩበት ቦታ ምድረበዳ እንደሆነ እያወቀ እግዚአብሄር ከሕዝቡ ጋራ ወተትና ማር ወደምታፈሰው ከነዓን አብሮ ካልሄደ በዚያው በምድረበዳ መኖሩን እንደሚመርጥ ይነግረዋል። ከዚህ ዓይነቱ የሙሴ ውሳኔ መማር የምንችለው እውነት ምንድነው?